# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 195 መጋቢት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የእምነት ተቋማት

## ሌብነትን ፊት ለፊት በመታገል ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል



ማሕሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን የመልካም አስተዳደር ችግርና ሌብነት ፊት ለፊት በመታገልና ለሕዝቡ አርአያ ሆኖ በመገኘት ረገድ ሁሉም የእምነት ተቋማት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የሃይማኖት መምህሩ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ አሳሰቡ፡፡ ሕዝበ ሙስሊሙ በተያዘው የረመዳን ፆም የተቸገሩትን በመርዳትና የሃገሪቱን ሰላምና አንድነት በማስጠበቅ ረገድ የበኩሉን ሚና ሊወጣ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደሀገር የመልካም አስተዳደርና የሌብነት ተግባር እየተስፋፋ መምጣቱ የሀገሪቱን ችግር ሆኗል፡፡ ለማኅበረሰባዊ ሥነ-ምግባር መላሸቅ በተለይም ቤተ እምነቶች በፈጣሪ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሚገባ መወጣት አለመቻላቸው አንዱ ምክንያት ነው፡፡

በተለያየ ቦታ ላይ በኃላፊነት ያስቀመጥናቸው


**የእምነት ተቋማት... ወደ ገጽ 11 ዞሯል**




# አቶ ጌታቸው ረዳ የትግራይ ክልል

## ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር ሆነው ተሾሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አቶ ጌታቸው ረዳን የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር አድርገው ሾሙ።

የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግስት አንቀጽ 62(9) እና በአዋጅ ቁጥር 359/1995 አንቀጽ 14/2/ለ መሠረት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲቋቋም ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት እንዲሁም በኢፌዲሪ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እና ግጭትን ለማስቆም በፕሪቶርያ


**አቶ ጌታቸው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን አስጀመሩ

ቃልኪዳን አሳዬ



አዲስ አበባ፡- ከንቲባ አዳነች አቤቤ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ በወራት ጊዜ ውስጥ ተገንብተው የሚጠናቀቁ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ግንባታ አስጀመሩ፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ በ300 ሚሊዮን ብር ወጪ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች በእንጦጦ አካባቢ ለሚገነባው የመኖሪያ ሕንፃ እና በተለያዩ የጉልበት ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ እናቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የእንጀራ መጋገሪያ ፋብሪካ፣ የተስፋ ብርሃን የማኅበረሰብ የምገባ ማዕከል፣ የሌማት ትሩፋትና ለሥራ እድል መፍጠሪያ የሚውል ባለ አራት ወለል አንድ ሕንጻ


**ከንቲባ አዳነች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**






















አቶ ክንፈ ኃይለማሪያም

## በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የድርቅና የጎርፍ አደጋዎች ተባብሰው ሊቀጥሉ ይችላሉ

**ታደሠ ብናልፋው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች እየተከሠቱ ያሉት የድርቅና የጎርፍ አደጋዎች በቀጣዮቹ ሳምንታትም ተባብሠው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጅ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳሬክተር አቶ ክንፈ ኃይለማሪያም በዓለም አቀፍ ለ62ኛ በኢትዮጵያ ለ42ኛ ጊዜ በሚከበረው የሚቲዎሮሎጂ ቀን ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ በተቋሙ የተሠሩ ጥናቶች የሚያሳዩት የድርቅና የጎርፍ አደጋዎች በሀገሪቱ በቀጣይም በይበልጥ ተጠናክረው ይከሰታሉ፡፡

ለዚህም የሚደርሰውን አደጋ ለመቋቋም የተጠናከረ የአየር ሁኔታ መከታተል፣ መተንበይና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን መገንባትና ማዘመንን ይገባል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም እየተከሰተ ያለውን የአየር ንብረት መዛባት ቀድሞ ለመተንበይ የሚያስችል ብሔራዊ የአየር ጠባይ አገልግሎት ማዕቀፍ በሀገሪቱ መዘርጋቱንና የተቋቋመው የብሔራዊ የአየር ንብረት ትንበያ ተጠናክሮ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገባ የባለድርሻ አካላት ርብርብ ያስፈልገዋል ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ ለማኅበራዊና ለኢኮኖሚ መሠረት የሆኑ የግብርና፣ የውሀ፣ የኢነርጂና የአደጋ ሥጋት ቅነሳ መርሐ ግብሮች በአየር ንብረት መዛባት ተፅዕኖ ስር ናቸው ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ በእነሱ ላይ የሚደርሠውን የአየር ንብረት መዛባት አደጋ ለመቀነስ ተቋሙ ጥናትና ክትትል የማድረግ ሥራ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በየጊዜው እየተነበየ የሚያቀርባቸውን የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎቶችን በማዘመን በጥራት ተደራሽ እንዲሆኑ በስፋት እየተሠራበት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በጥናቱ መሠረት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ይከሰታሉ ተብሎ የሚጠበቁት የአየር ንብረት መዛባት አደጋዎች ማለትም ጎርፍ፣ ድርቅና የመሳሰሉትን ለመቀነስ ተቋሙ ክትትልና ጥናት በማድረግ ኅብረተሰቡን ከአደጋ ለመከላከል በትኩረት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአየር ንብረት መዛባት የሚደርሰውን የተለያየ አደጋ በዘላቂነት ለመቋቋም ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ እንደሆነና ባለድርሻ አካላትም በርብርብ በአጋርነት እየሠሩ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

በቀጣይ አሥርት ዓመታት የአየር ጠባይ ለውጥ በሁሉም አህጉር እንደሚከሰት የተተነበየ መሆኑን ጠቁመው፤ የተጠናከረ የሙቀት ማዕበል፣ የተራዘሙ የሙቀት ወቅቶች፣ የቅዝቃዜ ወቅቶችም እንደሚኖሩ ተንብየዋል ብለዋል፡፡

አዳዲስ የአየር ሁኔታ ምልከታና ሞዴል ቴክኖሎጂ እያደጉ መምጣታቸው ውስብስብ የሆነውን የአየር ሁኔታና ጠባይ በተሻለ ለመገንዘብ ከማስቻላቸውም ባለፈ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት ለሁለት ቀን ይሰጥ በነበረበት የትንበያ ጥራት ልክ ዛሬም የአምስት ቀን ትንበያ መስጠት የሚከሰቱ ክስተቶችን ለመቀነስ ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የተፈጥሮ ሳይንስና የማኅበራዊ ሳይንስ የአየር ፀባይ ለውጥ ግዝፈት፣ ሂደቱንና ተጽዕኖውን በማጥናት የተሻለ የመቋቋም እና የመላመድ ዕድል እንዲኖር መሥራት አለባቸው ያሉት አቶ ክንፈ፤ የግሉ ዘርፍም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ላይ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

# ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በጋራ መሥራት ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የመንግሥት ተቋማትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች በጋራ መሥራት ይገባቸዋል ሲሉ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ "ብለ ብሎ ሩኸ ፋውንዴሽን" ከተባለ ድርጅት ጋር በ200 ሚሊዮን ብር ወጪ የሚተገበሩ የሕጻናት ፕሮጀክቶች ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት አካሂደዋል።

ዶክተር ኤርጎጌ እንደገለጹት፤ በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ከሚገጥሟቸው አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጫናዎች ለመታደግ የተቀናጀ ጥረት ያስፈልጋል።

የሕጻናት ጥቃትን በተመለከተ በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቅረፍ ተቋማትና ግለሰቦች እንዲሁም የተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በጋራ የሚያከናውናቸው ሥራዎች ወሳኝነታቸው የጎላ ነው ብለዋል።



ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ

ዶክተር ኤርጎጌ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ሕፃናትን የተመለከቱ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶችን ተፈፃሚ እንዲሆኑ ከመቀበል ባለፈ የሕፃናትን መብትና ማኅበራዊ ደህንነት ማስጠበቅ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ በሥራ ላይ እያዋለች ነው፡፡

ይሁንና በመንግሥት በኩል የሚከናወኑ ሥራዎች ብቻ በቂ አይደሉም ያሉት ሚኒስቴሯ፤ ከዚህ ባሻገር በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ግለሰቦች የሕጻናትን ሰብዓዊ መብት በማስጠበቅ ረገድ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያደርጉት ጥረት ማጠናከር አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

የብለ ብሎ ሩኸ ፋውንዴሽን የሀገር ውስጥ ዳይሬክተር ወይዘሮ ፀደይ ተፈራ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ ሕጻናትና ወጣቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

ፋውንዴሽኑ ሕጻናትን ተቀብሎ በመልካም ባሕሪ ከማሳደግ ባለፈ እድሜያቸው ከፍ ሲል የተለያዩ የሙያ ክህሎቶችን በማስተማር ብቁ ዜጋ ለማፍራት የበኩሉን ሚና እየተወጣ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ "ብለ ብሎ ሩኸ ፋውንዴሽን" ከተባለ ድርጅት ጋር በ200 ሚሊዮን ብር ወጪ የሚተገበሯቸው ፕሮጀክቶች በወላጅ አልባና የልዩ ፍላጎት ሕጻናት እንክብካቤና ሥልጠና ላይ ያተኮሩ ናቸው።



# ሸማቹ ማኅበረሰብ ለመብቱ እንዲታገል ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ሸማቹ ማኅበረሰብ በግብይት ወቅት የሚፈጸሙ የንግድ ጥሰቶችን መከላከል እንዲችልና ለመብቱ እንዲታገል ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል ሲል የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

"በደረሰኝ ግብይት ይፈጽሙ መብትዎን ያስከብሩ" በሚል መሪ ሃሳብ የሸማቾች መብት ቀን ትናንትና ሲከበር በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሸማቾች መብት ጥበቃና ግንዛቤ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይፉ አየለ እንደተናገሩት፤ በግብይት ወቅት የሚደርሱ የመብት ጥሰቶችን በሕግ አግባብ ብቻ መፍታት ስለማይቻል ሸማቹ መብቱን እንዲያስከብር ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል።

በተቋማት በኩል የንግድ ሥራ ጥሰቶች ሲፈጸሙ በሕግ አግባብ የማስተካከያ ዕርምጃ መውሰዱ እንደተጠበቀ ሆኖ አላስፈላጊ የግብይት ሂደቶችንና የዋጋ ጭማሪዎችን ለመከላከል ለመብቱ የሚታገልና ጥያቄ የሚነሳ ሸማች ማኅበረሰብ መፍጠር አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ሸማቹ መብቱን አውቆ ሲገዛ የማማረጥ ካልሆነውም የመተው በተጨማሪ በግብይቱ ጉዳቶች ሲደርስበት ካሳ የመጠየቅ መብት እንዳለው ጠቁመዋል።

በግብይት ሂደት ውስጥ ሸማቹ ጥራቱን የጠበቀና፣ ጊዜው ያላለፈበት ምርት በወቅታዊው ዋጋ የመግዛትና ከመረጠው የንግድ ተቋም የሚፈልገውን ምርት የመሸመት መብት አለው። ሸማቹ ለግብይት ሲወጣ መብቱን የማይጠቀም ከሆነ ደግሞ ነጋዴው እንደፈለገው የዋጋ ጭማሪ ሊያደርግ ይችላል ሲሉ ተናግረዋል።

ይሁንና ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቱን ጠንቅቆ ባለማወቁ የተነሳ የሕግ መብት ጥሰትን ሲከሰት ይስተዋላል። ሸማቹ ማኅበረሰብ የተቀመጠለትን መብት እንዲገነዘብ ሰፊ የንቅናቄ ሥራ መከናወን አለበት ብለዋል።

እንደ አቶ ሰይፉ ገለጻ፤ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ በ11 ክፍለ ከተማዎች የተለያዩ የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶችን በመጠቀም ለሸማቹ ማኅበረሰብ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሠርቷል፡፡

በዚህም ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቱን እንዲያውቅና በግብይት ወቅት ክፍተት ሲፈጠር ቅሬታውን ለማቅረብ ወዴት መሄድ እንዳለበት እንዲያውቅና በተሰጠው መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ጥረት መደረጉን አስረድተዋል፡፡

በግብይት ወቅት የሚፈጸሙ የሕግ ጥሰቶችን ለመከላከል ሸማቾች በደረሰኝ ግብይት ተጠቅመው መገበያየት ይኖርባቸዋል ያሉት አቶ ሰይፉ፤ ችግሮች በሚያጋጥሙት ወቅት የመብት ጥሰቶችን በሕጋዊ መንገድ ለመጠየቅ የደረሰኝ ግብይት ሚናው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ሸማቾች በደረሰኝ በሚገበያዩበት ወቅት 15 በመቶ ግብር መክፈል ይችላሉ። በተጨማሪ ለገዙት እቃ ሕጋዊ ባለቤት እንደሆኑ ማረጋገጫ ያገኛሉ ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በደረሰኝ መገበያየት የመንግሥትን ኢኮኖሚዊ እና ልማታዊ እንቅስቃሴ ከማሳደግ አንጻርም ከፍተኛ ድርሻ አለው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኅብረተሰቡም ከሕገወጥ የግብይት ሥርዓት በመውጣት የሸማቾችን መብት ለማስጠበቅ በደረሰኝ ግብይት ላይ የተመሠረተ ሕጋዊ አካሄድን መከተል ይኖርባቸዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የሸማቾች መብት ቀን በዓለም ደረጃ ለ40ኛ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ10ኛ ጊዜ ተከብሯል።

ዜና

# የተሻሻሉ የበግና የፍየል ዝርያዎች የአርሶ አደሩን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አሳድገዋል

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- የተሻሻሉ የበግና የፍየል ዝርያዎችን በምርምር በማዳቀል የአርሶአደሩን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ መቻሉን የአማራ ክልል ግብርና ምርምር አስታወቀ።

የአማራ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ጥላዬ ተክለወልድ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የምርምር ተቋሙ በእንስሳት ሀብት ላይ የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ነው።

ዶክተር ጥላዬ እንዳሉት ባሉት የምርምር ማዕከላት በእንስሳት ላይ ምርምሮችን በመሥራት የተሻሻሉ ዝርያዎች ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ እየተደረገ ነው። ኢንስቲትዩቱ በደብረ ብርሃን የግብርና ምርምር ማዕከል የበግ ዝርያዎች ላይ ምርምሮችን በመሥራት ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ እያደረገ ነው። ሀገር በቀል የሆኑ የበግ ዝርያዎችን በመረጣ የማሻሻል ሥራም ሠርቶ ውጤታማ ሆኗል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ የመንዝ በግ የዓመት ክብደቱ ከ17 ኪሎ ግራም የበለጠ አልነበረም። ይህን የመንዝ በግ በመረጣ በማሻሻል አሁን ላይ 24 ኪሎግራም ማድረስ የተቻለ ሲሆን በቀጣይም 29 ኪሎግራም ለማድረስ እየተሠራ ነው። በጣፋጭነቱ፤ በሽታን በመቋቋም ዝርያው በጣም ተወዳጅና ተመራጭ ነው። ዝርያውን ከሌላ ጋር ሳይቀላቀል ራሱን በመረጣ በማሻሻል ውጤታማ ሥራ ተሠርቷል ነው ያሉት።

ከስድስት ዓመት በፊት ማኅበረሰብ አቀፍ ዝርያ ማሻሻል ሥራ ውጤታማ በማድረግ ኢንስቲትዩቱ እውቅና እንደተሰጠው የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በመረጣ ብቻ ሳይሆን በማዳቀልም ውጤት ተገኝቷል ብለዋል። ‹‹ሀዋሲና ዶርተር›› የተባሉ ሁለት የበግ ዝርያዎችን ከውጭ በማምጣት ከአገር በቀል ዝርያዎች ጋር በመዳቀል ለአርሶአደሩ በማሰራጨት የአርሶአደሩ ተጠቃሚነት እንዲያድግ ተደርጓል። 50 በመቶ ‹‹ሀዋሲ›› የሚባል የእስራኤል የበግ ዝርያን 50 በመቶ ከሚሆን የመንዝ በግ ጋር በማዳቀል ክብደቱ 30 ኪሎግራም የሚመዝን በማድረግ በቀጥታ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ደረጃን ማሟላት አስችሏል ብለዋል።

ዝርያው አገር ውስጥም በገበያ ላይ የተሻለ ዋጋ የሚያስገኝ መሆኑን የተናገሩት ዶክተር ጥላዬ፤ የተዳቀለው በግ በቀንድ፤ በላትና በጣዕሙ ከመንዝ በግ ዝርያ የሚወስደው ዝርያ ስላለ ተመራጭ ነው። በተለይም ደቡብ ወሎ፤ ሰሜን ሸዋ፤ መንዝ፤ ሰሜን ወሎ መቄት፤ ለጋምቦ አካባቢ በእያንዳንዱ አርሶ አደር ላይ የሀዋሲ ዲቃላ በጎች ይገኛሉ። ይህም በገንዘብ ቢሰላ በትሪሊዮን ብር የሚቆጠር ነው። አርሶ አደሮች የተሻሻሉ ዝርያዎችን በመጠቀም ከራሳቸው አልፈው ለገበያ በማቅረብ ኢኮኖሚያቸውን በማሳደግ በከተሞች ዘመናዊ ቤት እስከመገንባት ደርሰዋል።

በለጋምቦ እስከ 75 በመቶ ሀዋሲ ዝርያና 25 በመቶ የወሎና የመንዝ ጥቁር በግ ዝርያ ያላቸው አውራ በጎችን ለሌሎች አካባቢ አርሶአደሮች በመሸጥ ገቢ እያገኙ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ፈጣን እድገትና ከፍተኛ መጠን የሥጋ ውጤት የሚያስገኝ ‹‹ዶርተር›› የሚባል የደቡብ አፍሪካና የኢራን የበግ ዝርያን በማዳቀል ክብደቱ 50 በመቶ በማሳደግ መልካም ውጤት አስገኝቷል። ጣፋጭና በሽታን መቋቋም የሚችል የበግ ዝርያ በመሆኑ በቆላማ አካባቢዎችና ደጋማ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶአደሮች ውጤታማ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ብለዋል።

የአበርገሌ የፍየል ዝርያዎችን በማሻሻል አርሶ አደሮች በማራባት የአርሶ አደሩ ገቢ እንዲሻሻል በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መምጣቱን የገለጹት ዶክተር ጥላዬ፤ በቀጣይ ውጤታማ የምርምር ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

# በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመንገድ ደህንነት ትምህርት ተግባራዊ እየተደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-የመንገድ ደህንነት ትምህርት በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑን የመንገድ ደህንነት መድህን ፈንድ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የመንገድ ደህንነት መድህን ፈንድ አገልግሎት ምክትል ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ፈቲያ ደግገባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የመንገድ ደህንነት ትምህርት ከሰባት እስከ ስምንት የትምህርት ዓይነቶች ላይ እንደ አንድ ርዕስ ተካቶ ለተማሪዎች በጥያቄ እና በንባብ መልክ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም የመንገድ ደህንነት ትምህርት በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው፡፡

እንደ ወይዘሮ ፈቲያ ገለጻ ትምህርቱ የአማራ ክልል ላይ አንዳንድ ቦታዎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ላይ የተጀመረ ሲሆን በኦሮሚያ ላይ ለማስጀመር በሂደት ላይ ነው፡፡

ከተያዘው ዓመት ጀምሮ በሁሉም ክልሎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ ቢሆንም አተገባበር ላይ ችግሮች መሆናቸውን የገለጹት ምክትል ሥራ አስፈጻሚዋ የክትትል እና ቁጥጥር እንዲሁም የመቀናጀት ሥራዎችን ለመሥራት መታቀዱን አስረድተዋል፡፡

ወይዘሮ ፈቲያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ በቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን ገልጸው በአዲስ አበባ ላይ በስምንት የትምህርት ዓይነቶች ላይ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህም የከተማው ትራንስፖርት አስተዳደር ኤጀንሲ በዘርፉ እየሠራ በመሆኑ ጥሩ አፈጻጸም መታየቱን አስረድተዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ትልቁ አደጋ የሚደርስበት በመሆኑ የመንገድ ደህንነት ትምህርቱን ለማስጀመር የሚያስችል



**ወይዘሮ ፈቲያ ደግገባ**

ውይይቶች ተጀምሯል ያሉት ምክትል ሥራ አስፈጻሚዋ በዚህም በክልል የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተግባራዊ መደረጉ የአደጋ መጠኑን ለመቀነስ የሚያስችል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የመንገድ ደህንነት ትምህርት በአስራ አንድ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ተካቶ ለ34ነጥብ 1 ሚሊዮን ተማሪዎች እና ለ22 ሚሊዮን ጎልማሶች በ2015 ዓ.ም በ50 ሺህ ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም፤በአሁኑ ወቅት በተማሪዎች ልክ የመንገድ ደህንነት ትምህርቱን ተደራሽ ለማድረግ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም በትምህርት ሥርዓቱ ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች እስከ ጎልማሶች ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ምክትል ሥራ አስኪያጅዋ ገልጸዋል፡፡

# የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር ፍላጎት የላቸውም

**አስመረት ብሥራት**

አዲስ አበባ፡- በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ሲያድጉ ግብር ከፋይ ስለሚሆኑና ይጠቀሙበት የነበረውን ሼድ ስለሚለቁ እድገቱን እንደማይፈልጉት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጳውሎስ በርጋ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በአነስተኛና ጥቃቅን ልማት የተሠማሩት አንቀሳቃሾች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ሲሸጋገሩ ከሚጠበቅባቸው ግብር ከፋይነት በላይም የመሥሪያ ሼዱን ስለሚለቁ ከማደግ ይልቅ እዚያው መቆየትን ምርጫቸው ያደርጋሉ።

ከዚህ የተሳሳተ አስተሳሰብ እንዲወጡም የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበኩሉን ጥረት እያደረገ መሆኑን አመልክተው፤ በአሁኑ ጊዜም የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጠንካራ የሥራ ፈጣሪነት ሥነ ልቦና እንዲኖራቸውና ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ በመሸጋገራቸው ግብር መክፈልና ሼዳቸውን መልቀቅ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ ዕድልም ይዞ እንደሚመጣላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እየሰጠ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አብዛኛዎቹ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ካሉባቸው በርካታ ተግዳሮቶች መካከል የፋይናንስ አቅርቦት ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳል ያሉት አቶ ጳውሎስ ፤ በዚህ ረገድ ያለው ችግር እጥረት መኖር ብቻ ሳይሆን ለብድር ዋስትና ማስያዣነት አምራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት መስፈርትም ካለው ነባራዊ ሁኔታና ከአምራቾች አቅም አንጻር ሲመዘን ተገቢ አለመሆኑን ተናግረዋል።

ብድር ለመበደር ከሚፈልጉት መጠን ከሁለት እስከ ሰባት በመቶ ተቀማጭ እንዲኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህንን በዓይነት ለማስያዝ የሚፈልጉ ደግሞ ቤትና መኪና ብቻ በዋስትና ማስያዣ የሚፈቀድላቸው መሆኑን አስረድተዋል።

በዓመታት እቅድ ውስጥ ጥሪት ቋጥሮ፤ ራሱን ችሎ ሀብት ወደ ማፍራት ብሎም መኪናና ቤት ለመግዛት ለሚውተረተር አምራች ይሄ እንኳን የሚሞከር የሚታሰብም አለመሆኑን ተናግረዋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፎ ለመበደር እድሉን የሚያገኙ አምራቾች ቢኖሩ እንኳን ወለዱ 18 በመቶ የሚደርስ በመሆኑ ሠርተው ለመለወጥ ላሰቡ ጀማሪዎች እጅግ አዳጋች መሆኑን ገልጸዋል።

ኢንዱስትሪው እንደ አጠቃላይ ካለበት ችግር ስልሳ በመቶውን ድርሻ የሚይዘው የግብዓት እጥረት ሲሆን ዛሬም ቢሆን በአብዛኛዎቹ አምራቾች የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በዶላር እንደ ሕንድና ቻይና ከመሳሰሉ ሀገራት ተገዝተው በሚመጡ ጥሬ እቃዎችና መለዋወጫዎች መሆኑን አመልክተዋል።

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለአምራች ኢንተርፕራይዝ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ፈተና መሆኑን ያነሱት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ የውጭ ምንዛሪ ከባንኮች እየጠበቁ ከመቆየት ይልቅ የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኝ የሚያስችል መንገድ ካለ ማማተርና ያለውንም የውጭ ምንዛሪ በአግባቡ ቅድሚያ ለሚሰጠው ጉዳይ ብቻ በቁጠባ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በማምረት ረገድም ሰፊ ክፍተት አለ ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ ኢንተርፕራይዞች እየሠሩ ያሉት ከማምረት አቅማቸው 50 በመቶ ብቻ መሆኑን አስታውቀዋል። በገበያው ውስጥ እንዲቆዩ የሚረዳቸው በዋናነት ገበያው ውድድር የሌለበት በመሆኑና እጥረት በመኖሩ ሲሆን፣ በአቅማቸው ልክ ባለማምረታቸው የሚጨምረውን የማምረቻ ዋጋ የሚያካክሱት በተገልጋዩ ላይ ዋጋ በመጨመር መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ሀገር በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተደራጁ እንደ ሕፃናት ልጅ እንክብካቤ የሚፈልጉ አንቀሳቃሾች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ እነርሱ በቀላሉ ተስፋ ቆርጠው ስራውን እንዳያቆሙ በተቻለ መጠን ሥልጠናና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት ይደረጋል ብለዋል። በሚሠማሩበት የሙያ መስክ እውቀት ሳይኖራቸው ወደ ሥራ የሚገቡና ብሩን ለማግኘት ብቻ የሚደራጁ አንቀሳቃሾች የመክሰም ዕድላቸው ሰፊ መሆኑንም ተናግረዋል።

ዜና

# አቶ ጌታቸው ረዳ የትግራይ ክልል ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ደቡብ አፍሪካ በተደረገው የሠላም ስምምነት አንቀጽ 10(1) መሠረት አካታች ጊዜያዊ አስተዳደር ማቋቋም በማስፈለጉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 9 ቀን 2015 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የትግራይ ክልል አካታች ጊዜያዊ አስተዳደር ደንብን አጽድቋል፡፡

በዚሁ ደንብ አንቀጽ 3(2) መሠረትም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በትናንትናው እለት አቶ ጌታቸው ረዳን የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር አድርገው መሾማቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በማኅበራዊ ትስስር ገጹ አስታውቋል።

ርዕሰ መስተዳደሩ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎችን ውክልና የሚያረጋግጥ እና አካታች የሆነ አስተዳደር በማዋቀር የክልሉን አስፈፃሚ አካል የመምራት እና የማስተባበር ኃላፊነት የተጣለባቸው መሆኑንም ጽሕፈት ቤቱ አስታውቋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከትናንት በስቲያ ባካሄደው ስድስተኛ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለተኛ ዓመት አንደኛ ልዩ ጉባዔው ሕወሓትን ከሽብርተኝነት መዝገብ ላይ ማንሳቱ የሚታወስ ነው፡፡ ይህም በትግራይ ሁሉንም አካታች ጊዜያዊ አስተዳደር ለማቋቋም እንደሚረዳ ተነግሯል።

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2ኛ ዓመት 1ኛ ልዩ ጉባኤውን ሲያካሂድ የፍትሕ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶክተር)፤ ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ፍረጃ ማንሳት በትግራይ አካታች የጊዜያዊ አስተዳደር ለማቋቋም ታስበው ለሚከናወኑ ሥራዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት አንቀጽ 7/2 C መሠረት የፌዴራል መንግሥት በሕወሓት ላይ የተጣለውን የሽብርተኝነት ስያሜ በምክር ቤቱ እንዲነሳ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻች ተገልጿል።

በትግራይ ሕጋዊ ምርጫ ተካሂዶ መደበኛ አስተዳደር እስኪቋቋም ድረስ በጊዜያዊነት እንዲሠራ በቀረበ አስተዳደር ውስጥ ደግሞ ሕወሓት ያለበት በመሆኑ በምክር ቤቱ ከዚህ ቀደም ሕወሓት ላይ የተወሰነውን የሽብርተኝነት ውሳኔ ማንሳቱ የሰላም ስምምነቱ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲፈጸም ይረዳል ብለዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ ቤልጅጌ ባቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ፤ በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት የሕወሓት ኢ-ሕገመንግሥታዊ እንቅስቃሴ እንዲቀለበስ መደረጉን ጠቁመው፤ ስምምነቱን ተከትሎ አሁን ላይ ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ማንሳቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

በፕሪቶርያው ስምምነት አንቀጽ 10/1 መሰረት የሕዝብ ተወካዮችና የትግራይ ክልል ምክር ቤት ምርጫ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካኝነት እስኪከናወን ድረስ አካታች ጊዜያዊ መንግሥት እንደሚመሠረት ተገልጿል።

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄደው 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 13ኛ መደበኛ ስብሰባ ሕወሓትን አሸባሪ ብሎ መሠየሙ የሚታወስ ነው፡፡

# ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከግማሽ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ግንባታም ተጀምሯል፡፡

ማዕከሉ ባለ 10 ወለል ሕንጻ ሲሆን በውስጡ 100 የሚሆኑ መኖሪያ ቤቶችን የያዘ ነው፡፡ የግንባታው ወጪ ሙሉ ለሙሉ በከተማ አስተዳደሩ የሚሸፈን ነው ተብሏል፡፡

በተጨማሪም ከንቲባዋ በክፍለ ከተማው በወረዳ 8 በድል በር አካባቢ በመንግሥትና በግል አጋርነት በ70/30 መርሐ ግብር ግንባታው በ90 ቀናት የሚጠናቀቅ የሁለት ብሎክ አፓርትመንት የG+12 መኖሪያ ሕንፃ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ በማስቀመጥ ግንባታውን አስጀምረዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የፕሮጀክቶቹን ግንባታ መሠረት ድንጋይ ባስቀመጡበት ጊዜ እንደገለጹት ከጉለሌ ክፍለ ከተማ አንገብጋቢ ጥያቄዎች መካከል የቤት ችግር አንዱ ነው። የተጀመሩት ፕሮጀክቶች እንጨት ለቅመው በጽናትና በትጋት ልጆቻቸውን ለሚያሳድጉ እናቶች እና የመሥሪያ ቦታ ችግር ያለባቸው ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና በክፍለ ከተማው ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር የሚያቃልሉ ናቸው ብለዋል።

ፕሮጀክቶቹ በሁሉም የከተማዋ አካባቢዎች የሚኖሩ ነዋሪዎችን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው ያሉት ከንቲባ አዳነች በቅርበት ክትትል በማድረግ እና ፕሮጀክቶቹን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ እናደርጋለንም ብለዋል።

የፕሮጀክቶቹ መገንባት የነዋሪዎችን መሠረታዊ የኑሮ ሁኔታን የሚያቃልሉ መሆናቸውን የገለጹት ከንቲባዋ፤ለፕሮጀክቶቹ ተፈጻሚነት ሁሉም ባለድርሻ አካላትና የአካባቢው ማኅበረሰብ እገዛ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ አሜጋ በበኩላቸው በክፍለ ከተማው ካለው የነዋሪዎች ቁጥር አንጻር የመሠረታዊ ፍላጎት አቅርቦቱ አነስተኛ ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም ከንቲባዋ ያስጀመሯቸው ፕሮጀክቶች የአካባቢውን ማኅበረሰብ ኑሮ በማቃለልና የሥራ ባሕልን በማዳበር ረገድ የጎላ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል።

ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ከዚህ በፊት በከንቲባዋ ቃል በተገባው መሠረት በማኅበረሰቡ ዘንድ በስፋት ይጠየቅ የነበረው የውሃ አቅርቦት ችግርን የሚያቃልል ሁለት የውሃ ቦቴ ተሽከርካሪዎችን ከንቲባዋ ለክፍለ ከተማው አስረክበዋል። በተጨማሪም በክፍለ ከተማው ሥር ባሉ ጤና ጣቢያዎች የሚነሳውን የአምቡላንስ እጥረት ለማቃለል የሁለት አምቡላንሶች የቁልፍ ርክክብ መደረጉን አቶ ተስፋዬ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ተስፋዬ ገለጻ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የከተማይቱን ብሎም የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎች ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ፀጥታን ለማደፍረስ በተደራጀ ሁኔታ በእምነት፣ በብሔር፤ በሰንደቅ ዓላማና በመዝሙር ስም የሚንቀሳቀሱ አካላት መኖራቸው ታውቋል፡፡

እነዚህ ኃይሎች ዋነኛ ዓላማቸው በተሳሳተና በስውር የፖለቲካ አጀንዳ ወጣቶችን በስሜት በማነሳሳት እኩይ የፖለቲካ አጀንዳዎቻቸውን በማሳካት በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለመተማመንንና፣ ጥርጣሬን እንዲሁም በሕዝቡ ዘንድ ቅሬታን እና ቁርሾ በመፍጠር የልማትና የእድገት ጉዞን ለማደናቀፍ ያደረጉት ሙከራ በተደረገው ከፍተኛ ትግል ሳይሳካ መቅረቱን ጠቁመዋል፡፡

የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጫና የግንባታ ማስጀመሪያ ሥነሥርዓቱ ላይ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ አሜጋ፣ የተለያዩ የሀይማኖት አባቶችና የመዲናዋ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ከረመዳን ወር ትሩፋቶች እንቋደስ!

ረመዳን በእስልምና ዘመን አቆጣጠር 12 ወራቶች ውስጥ አንደኛውና በቅዱስ ቁርዓን ጾም ግዴታ የተደረገበት ወር ነው። ከእስልምና መሰረታዊ መመሪያዎች ውስጥ የረመዳንን ፆም መፆም ዋነኛው ሲሆን ማንኛውም አቅም ያለው፤ ጤነኛ የሆነ ሰው፤ እድሜው የደረሰ መፆም ይገደዳል። ይህም ጎህ ከቀደደችበት ጊዜ ጀምሮ ፀሐይ እስከምትጠልቅ ድረስ የሚፈጸም የፆም ተግባር ነው። በአጠቃላይ የእምነቱ መሰረት ስለሆነ ፆም ግዴታ ነው።

የረመዳን ፆም ለፈጣሪ ያለን ታዛዥነት ውስጣችን ታማኝነት፣ ርህራሄና ይቅርባይነት የምናሳይበት ነው። በተለይ ባሳለፍናቸው ወራቶች ውስጥ በንግግራችንና በተግባራችን የተገለፁ ጥፋቶች፤ ከፈጣሪ ያፈነገጡ ተግባራት፣ የእምቢተኝነት ባህሪያት፣ በሰው ላይ የፈጸምናቸውን ትክልል ያልሆኑ ድርጊቶች በማስታወስ የምንጸጸትበትና በአጠቃላይ ፆም የተበላሹብንን ነገሮች ለማስተካከልና ራሳችንን በትክክለኛ መንገድ ለማነፅና ወደ አዲስ ምዕራፍ ለመሸጋገር የሚረዳ መንፈሳዊ ማሰልጠኛ ማዕከል ነው። ስለዚህም ከግለሰብ እስከ ሀገር ድረስ የተፈጸሙ ስህተቶች ካሉ መለስ ብለን የምናይበትና የእርምት እርምጃ የምንወስድበት ጊዜ ነው።

ረመዳን የእዝነት ወር ነው። ይህም ማለት እርስበርስ የመተዛዘን፤ የመረዳዳት፤ የመደጋገፍ ወቅት ነው። በተለይም ደግሞ አብሮነት፤ መተጋገዝ፤ መረዳዳት የኢትዮጵያውያኖች አንዱ መገለጫ ነው። የረመዳን ወርም ሙስሊሙ ኅብረተሰብ የእምነቱ ግዴታ የሆነውን ዘካውን (አስራቱን) የሚወጣበት ነው። እንደሚታወቀው ማንኛውም አቅም ያለው ሰው ዘካ ይሰጣል፤ ወይም ካለው ገንዘብ ላይ ላጡ ለነጡ ወገኖቹ ያካፍላል። ይህንን በጎ ተግባር መፈጸም በተለይም በረመዳን ወር ከእያንዳንዱ ሙስሊም ይጠበቃል።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በድርቅ የተጎዱ፤ በግጭት የተፈናቀሉ ወገኖች በየቦታው ይገኛሉ። እነዚህን ወገኖች መደገፍ ደግሞ ኃይማኖታዊም ሆነ የዜግነት ግዴታ ጭምር ነው። በረመዳን ወር የሚሰጠውም ዘካ (ምፅዋት) አንዱ ዓላማም ዝም ብሎ መስጠት ብቻ ሳይሆን ሰዎችን እያቋቋሙ አዲስ ምዕራፍ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነው። ሰዎች ከችግርና ከተረጂነት የሚወጡበትን ስርዓት ለማበጀት ዘካ በአግባቡ እንዲሰጥ ነው እስልምና የሚያዘው። ዘካ ድህነትን ለመከላከል እስልምና እንደመፍትሔ ካቀረባቸው መንገዶች አንዱ ነውና በሁሉም አካባቢ የተቸገሩና የታረዙ ወገኖች በመርዳት የረመዳንን አጅር (ትሩፋት) ልናገኝ ይገባል።

የእስልምና እምነት ካለን ሃብት 2 ነጥብ5 በመቶ የሚሆነውን ለተቸገሩ እንድንሰጥ ያዘናል። ይህም ደግሞ ለትክክለኛው ዓላማ መዋል ስላለበት ተበታትኖ ሳይሆን በተደራጀ መልኩ ለባለቤቶቹ ደርሶ ሰዎች እንዲለወጡበትና ከተረጂነት ወደ ረጂነት እንዲሸጋገሩ፤ ስራ ላይ ውጤታማ የሚሆኑበትን የማቋቋም ስራ መስራት ያስፈልጋል። በተለይም አሁን በሀገራችን ላይ ከተከሰተው ድርቅ፣ ረሃብ፣ መፈናቀል፣ የተነሳ በርካታ ወገኖች በአስከፊ ችግር ውስጥ የሚገኙ በመሆኑ ከተለያዩ ወገኖች ዘካዎችን (ምጽዋቶችን) በማሰባሰብ ለወገን መድረስ ከሙስሊሙ ኅብረተሰብ የሚጠበቅ ነው።

ቅዱስ ቁርዓን «ለጎረቤቱ የማያዝን ሰው አማኝ አይደለም» ይላል። ጎረቤቱ ተርቦ እሱ ጠግቦ ያደረ ሰው እንደለመነ ነው የሚቆጠረው። ስለዚህም በየቦታው ተቸግረው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን መርዳት በረመዳን ወቅት ከሚጠበቁ በጎ ተግባራት ውስጥ አንዱ ሊሆን ይገባል።

በርካታ ኢትዮጵያውያን በድርቅ፤ በግጭት፤ በመፈናቀልና በስደት ምክንያት ተርበዋል፤ እንስሳቶቻቸውን አጥተዋል፤ ማሳዎቻቸው ፍሬ አጥተዋል፤ እነሱም ሆኑ ልጆቻቸው ተርበዋል፤ ታርዘዋል። ስለዚህም ለእነዚህ ወገኖች መድረስ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም።

ዛሬ የተቸገሩት ወገኖቻችን ትናንት ሰጪዎች ነበሩ። ዛሬ የተራቡት ወገኖቻችን ትላንት ከራሳቸው አልፈው ብዙዎችን አጥግበው ሲያሳድሩ ኖረዋል። ስለዚህም በዚህ በተቀደሰው የረመዳን ወር ዛሬ እኛ መከታ ልንሆናቸው ይገባል። የመረዳዳት፤ የአብሮነት፤ የመተዛዘን ወር በሆነው በረመዳን ወቅትም የሚጠበቀው ይኸው ናውና!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከብሔራዊ ቡድኑ ጎን የመቆም ትክክለኛው ጊዜ ዛሬ ነው

ብርሃን ፈይሳ

በቅርቡ በተካሄደው የኳታር ዓለም ዋንጫ ድንቅ አቋም ከነበራቸውና ለዋንጫም ይጠበቁ ከነበሩ ቡድኖች መካከል አንዱ የክሮሺያ ብሔራዊ ቡድን መሆኑ የሚታወስ ነው። በወቅቱ ክሮሺያ ቡድኗ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ሲፈጽም፤ ወደ ግማሽ ማጣሪያ ያለፈው በእግር ኳስ ታሪክ የደመቀና ግዙፍ ታሪክ ያላትን ብራዚልን በመለያ ምት ከውድድር ውጪ በማድረግም ጭምር ነበር። እግር ኳስ እጅግ እንዲወደድ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ይህ አንዱ ነው።

በብርቅዬው ዋልያ የተሰየመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን በአህጉረ አፍሪካ ታላቅ በሚባለው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ለመካፈል የማጣሪያ ውድድሩን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከውድድሩ ጥንስስ አንስቶ አህጉር አቀፉን የእግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን በማቅናት ከፍተኛ ሚና የነበራት ኢትዮጵያ ከመድረኩ ከራቀች ከዓመታት በኋላ መመለስ መቻሏ እግር ኳስ ወዳዱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማስደሰቱ አይካድም። ዘንድሮም ዳግም በመድረኩ ተወዳዳሪ ለመሆን የማጣሪያ ጉዞውን በማላዊ ሽንፈት የጀመረች ቢሆንም ሽንፈቱን በቀናት ልዩነት ቀልብሳ ትልቅ ግምት የተሰጣት ግብጽ ላይ የሁለት ለምንም ጣፋጭ ድል ማጣጣሟ አይዘነጋም። ሶስተኛ የማጣሪያ ጨዋታዋን ደግሞ ዛሬ የጊኒ አቻዋን በገለልተኛ ሜዳ ሞሮኮ ላይ ትገጥማለች። ጊኒ ልክ እንደ ፈርኦኖቹ ሁሉ ትልቅ ግምት የተሰጣት አገር ብትሆንም እግር ኳስ ነውና የቀደመ ታሪክ ሳይሆን ጠንካራ የቡድን ስራ የዋሊያዎቹን ዓላማ ያሳካል የሚል ተስፋም በብዙዎች ዘንድ አድሯል።

በእርግጥ ኢትዮጵያ በስፖርቱ የሚጠቀስ ጠንካራ ስም የላትም፤ ነገር ግን እግር ኳስ እንደ ሀገር እጅግ ተወዳጅና ደጋፊውም ያለውን ሁሉ የሰጠው ስፖርት ነውና ዋልያዎቹ ትልቅ የሞራል ስንቅ ሁሌም አብሯቸው አለ።

አሁን ላይ ኢትዮጵያዊ ስሜትን ከሚያነቃቁ፣ አንድነታችንንም ከሚመልሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ እግር ኳስ ነው። ለዚህም ከሁለት ዓመታት አስቀድሞ ካሜሮን አዘጋጅ በነበረችበት የአፍሪካ ዋንጫ የማለፋችን ብስራት ሲሰማ ያሳደረብንን አገራዊ ስሜት ማስታወስ በቂ ነው። በመሆኑም እንደቀደመው ጊዜ በረጅም ሳይሆን በአጭር ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፏችንን ለማረጋገጥ ለዚህ ማጣሪያ ውድድር ትኩረት መስጠት አለብን። የኢትዮጵያን ስኬታማ የእግር ኳስ ታሪክ ዛሬ ያውም አሁን ባለንበት ሁኔታ መጻፍ መጀመር እንችላለን። ክሮሺያ ነጻነቷን ባወጀች ማግስት ነበር ብሔራዊ ቡድኗ እውቅና ያገኘላት ዘንድ ፌዴሬሽን አዋቅራ የአህጉርና ዓለም አቀፉን እግር ኳስ ለሚመሩት አካላት ጥያቄዋን ያቀረበችው። ከሶስት ዓመት በኋላም እአአ 1996 የአውሮፓ ዋንጫ የዋንጫ ተፋላሚ በመሆን ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቀቀች። ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ፈረንሳይ ባዘጋጀችው የዓለም ዋንጫ የመጀመሪያውን ተሳትፎ በማድረግ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ በማጠናቀቅ የውድድሩ ክስተት ለመሆን በቃች። በመሃል ጥቂት ብትዳከምም በ2018 የሩሲያ የዓለም ዋንጫ በድጋሚ ክስተት የሆነ ቡድኗን ይዛ በመቅረብ፤ በፈረንሳይ ተሸንፋ ለጥቂት ዋንጫው አመለጣት። በኳታርም ከአስፈሪ ቡድኖች መካከል አንዱ ነበር። እኛም ከዚህ መማር አለብን።

በማጣሪያው ሁለተኛ ጨዋታ ኢትዮጵያ በሰባት የአፍሪካ ዋንጫዎች የተንቆጠቆጠችውንና ከአህጉሩ ጠንካራ የእግር ኳስ ቡድኖች መካከል አንዷ ከሆነችው ከግብጽ በተገናኘችበት ወቅት፤ የተመዘገበው ውጤት የፈጠረው መነቃቃት የሚታወስ ነው። ይህ የሆነው ቡድኑ ባደረገው ርብርብ እንደመሆኑ፤ አሁንም ስህተቶቹን በማረም መጫወት ይጠበቅበታል። ጥሩ እግር ኳስን ከመጫወት አቅም ባለፈ አሁን ላይ ለሽንፈትና ውጤት ማጣት በሰፋት የሚነሳው የሜዳ ጉዳይም በዚህ ማጣሪያ እንከን ሊሆን አይገባም። በእርግጥ በራስ ሜዳ፣ በሚያውቁት የአየር ሁኔታ ውስጥ በደጋፊ ታጅቦ መጫወት በራስ የመተማመን ስሜትን ይፈጥራል። ከእነዚህ ሁኔታዎች ርቆ መጫወትም የራሱ ተጽእኖ እንዳለው የማይካድ ሃቅ ነው።

አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ዋሊያዎቹን ወደ መምራት ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ሀገራቸው ላይ ያደረጓቸው ዓለም አቀፍ ጨዋታዎች አራት ብቻ ናቸው። የተቀሩትን ጨዋታዎች በሙሉ ከኢትዮጵያ ውጭ በውሰት ሜዳዎች ላይ አከናውነዋል። ይህ ምናልባትም አስቸጋሪ ሁኔታ ሊመስል ይችላል፤ ይሁንና ዋሊያዎቹ በዚህ መልኩ እየተጫወቱ ከስምንት ዓመታት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ እንዲሁም ከስድስት ዓመታት በኋላ ወደ ቻን (ምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ) ማለፍ ችለዋል። በመሆኑም ቡድኑ ችግሮቹን ብቻም ሳይሆን መልካም ሁኔታዎችንም በመጠቀም አንጻራዊ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ነው። አሁንም እንደ አዲስ የሜዳ ችግርን እና ከደጋፊ መራቅን እንደ ምክንያት ከማስቀመጥ ይልቅ በምን መልኩ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል የሚለውን እያሰቡ መጓዝ ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል።

ከሶስት አስርት ዓመታት ያልበለጠ እድሜ ያላት ትንሿ ሀገር ክሮሺያ ከዩጎዝላቪያ ተነጥላ ነጻነቷን ለማወጅ ከአራት ዓመት በላይ ጦርነት ውስጥ ቆይታለች፤ ዜጎቿም ተሰደው ነበር። ይሁንና ያለፉትን መጥፎ ጊዜያት በማሰብ ሳይሆን ሀገርን የሚያኮሩ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን በማፍራት ላይ ማተኮሯ ትልቅ የእግር ኳስ አገር አድርጓታል። ክሮሺያዊው የስፖርት ጋዜጠኛ ስርዳን ፋቢጃንክ «እግር ኳስን ያገኘነው በደም ነው። ምንም እንኳን ትንሽ ሀገር ብንሆንም ሁሌም የእግር ኳስ ቡድናችን ካለበት ልቆ እንዲገኝ ጥረት እናደርጋለን። ብሔራዊ ጀግኖቻችን የሆኑት ተጫዋቾችም ያላቸውን ኃይል አሟጠው ነው የሚጫወቱት» ሲል በአንድ ወቅት ተናግሮ ነበር።

በእርግጥም አንድ ቡድን ጠንካራ አሊያም ስኬታማ ነው ሊያሰኙት ከሚችሉት ነገሮች መካከል አንዱ ራስን ከሁኔታዎች ጋር አስማምቶ መገኘቱ ነው። የቡድኑ አባላት እንደ ክሮሺያዊያን ለየትኛውም ጨዋታ ትኩረት በመስጠትና ኢትዮጵያን ብቻ በማሰብ የአሸናፊነት ስነልቦናን ተላብሶ መሰለፍ ያስፈልጋል። ምድቡን እየመራ የሚገኘው ቡድኑ በቀጣይ የሚኖሩት ጨዋታዎች እየጠነከሩበት እንደሚሄዱ ግልጽ በመሆኑ ከወዲሁ ነጥቡን በማስጠበቅ ለአምስተኛና ስድስተኛ ጨዋታዎች ምቹ መደላድልን መፍጠር አስፈላጊ ነው።

በበርካታ ቡድኖች መልበሻ ቤት የሚስተዋለው አላስፈላጊ ሁኔታ በክሮሺያ ብሔራዊ ቡድን ቦታ እንደሌለው ጋዜጠኛው ፋቢጃንክ ይገልጻል። አንድም ሰው ከቡድኑ በላይ ሊሆን እንደማይችልና ሁሉም በስርዓት እንደሚከናወንም ይጠቁማል። ሀገርን በሚመለከት ጉዳይ የትኞቹም ግላዊ ሁኔታዎች ቦታ የላቸውም። ከቻን ውድድር አንስቶ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾችና አሰልጣኙ መካከል የተስተዋለው ሁኔታም መፈታት የሚገባው ነው። ብሔራዊ ቡድን ከሀገር መከላከያ ሊለይ የሚችለው በሚውሉበት አውድ እንጂ ግልጋሎታቸው የሀገርን ስም ማስጠራት እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ተጫዋች የቀረበለትን ጥሪ አክብሮ በተጠንቀቅ ሊቆም ይገባዋል። በአንጻሩ ኢትዮጵያን የሚያህል ሀገር ተሸክሞ የሚጫወትን ቡድን የሚመሩት አሰልጣኝ ስርዓት እንዲከበር ማድረጋቸው የሚያስመሰግናቸው ተግባር ሆኖ ሳለ ሆደ ሰፊ መሆንም ይጠበቅባቸዋል። አንድነትና ትልቅ አገራዊ ስሜት መፍጠር ከቻሉም በየትኛውም ቡድን በእግር ኳሳዊ ምክንያት ተበልጠው እንኳን ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉበት እድል ይኖራል። ለዚህም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከዋልያዎቹ ጎን ቆሞ በሞራል ሊደግፍ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ

# ግብርናውን ከኋላቀርነት ለዘለቄታው ለማላቀቅ

**ዳግም ከበደ**

አገራችን ኢትዮጵያ ከሶስት ሺህ ዘመናት ዘለግ ያለ የስልጣኔ ታሪክ ባለቤት በአገረ መንግስት ግንባታና ሉዓላዊነትን ጠብቆ በመኖርም ጥቂት ከሚባሉ አገራት ቀዳሚዋ ነች። በአንድነት፣ በቀደምት ስልጣኔና ለጠላት እጅ ባለመስጠት ብቸኛ ምስራቅ አፍሪካዊት የጥቁር ሕዝቦች ኩራት መሆኗም በልጆቿ ብቻ ሳይሆን ከሌላኛው የዓለም ክፍል በመጡ የውጭ አገር አሳሾችና የታሪክ ፀሐፊያን የተመሰከረ ጥሬ ሃቅ ነው።

ይህ መልካም ታሪካችን ሳይበረዝና ሳይከለስ ታሪክ ይመዝግበው እንጂ በሌላኛው ጎን ግን መልካም ጎናችንን ለማጠልሸት የሚገዳደሩ፣ ጥንካሬያችንን የሚፈትኑ የቀደመ ኃያልነታችን ላይ ጥቁር ጥላ የጋረዱ ክፍተቶች አሉብን። ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል በዘመናት ጊዜ ውስጥ የሚከሰት ድርቅና ረሃብ አንዱ ነው።

በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ላይ የድርቅ መከሰት ተፈጥሯዊና የሚጠበቅ ቢሆንም ፤ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ችግር የሚከሰትን ድርቅ መቋቋም የሚችል ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት ግን ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ እንደኛ ባሉ ሀገራት የግብርናውን ዘርፍ ከማዘመን ጀምሮ ሀገራዊ የሰው ኃይልን እና የተፈጥሮ ሀብትን ውጤታማ በሆነ መልኩ አቀናጅቶ መጓዝን የሚጠይቅ ነው።

ጠንካራ የስራ ባህል ማዳበር፣ ዜጎችን ለአንድ አላማ በማስተባበር አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አቅም መፍጠር ድርቅንና ከድርቅ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ለዘለቄታው በመቋቋም ሊያስከትል የሚችለውን ሰብዓዊ ሆነ ምጣኔ ሀብታዊ ጥፋት መቋቋም ይቻላል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ድርቅ ወደ ከፋ ረሃብ ተሸጋግሮ በሰው፣ በቤት በዱር እንስሳት ላይ ሊያስከትል የሚችለው እልቂት የከፋ ነው። እንደ ሀገርም በየወቅቱ መሰል ጥቁር ጠባሳዎችን ያስተናገድን እንደመሆናችን ለክስተቱ አዲስ አይደለንም።

ዋናው አሳሳቢው ጉዳይ ግን ተደጋግሞ የሚከሰትን ድርቅ በሕዝባችን ላይ የከፋ ጉዳት ሳያስከትል እንዴት መቋቋም እንችላለን የሚለውን ጥያቄ እስካሁን ድረስ መመለስ አለመቻላችን ነው። በዚህ ምክንያት በየጊዜው በርካታ ሚሊዮን ዜጎች የሚሰሩ እጆች ይዘው የተፈጥሮን ቁጣ መቋቋም አቅቷቸው እጃቸውን ለምፅዋት ሲዘረጉ እናያለን።

አሁንም ድረስ ይነስ ይብዛ ሰፋፊ መሬትና ጉልበት ይዘው ከሰማይ የሚወርድ ዝናብና ከምእራባውያን የሚዘረጋ ምፅዋት የሚጠብቁ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ቁጥራቸው ጥቂት የሚባል አይደለም።

ተፈጥሮ ስትጨክንብን፣ የሰማይ ማማዎች ሲነጥፉ ወትሮውንም ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ለእርሻ ተግባር ሳይሆን ለጉሮሯቸው ማርጠቢያ ጠብታ ውሃ የማጣታቸው እውነታ እንግዳ ክስተት አይደለም። በዚህም የሚያጋጥሙ ችግሮች መልካቸው ብዙ ነው። የሚበላ እና የሚጠጣ ማጣት፤ ነገዎች ላይ ተስፋ መቁረጥና በሌሎች ምጽዋት ዛሬን መግፋት ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው።

ከሰሞኑ በሀገራችን በኦሮሚያ በደቡብና በሶማሌ ክልሎች ያጋጠመውም ይሄው ነው። ችግሩ ተከታታይ የዝናብ ወቅቶች ዝናብ ባለመስጠታቸው የተከሰተ ቢሆንም፤ ችግሩ ከጅምሩ ትኩረት ተሰጥቶት መፍትሄ እየተቀመጠለት ባለመምጣቱ ዛሬ አስቸኳይ መፍትሄ በማፈላለግ ተጠምደናል።

መንግስት የሀገርን ሉዓላዊነትና ጥቅም፣ ሰላምና ፀጥታ ከማስከበር ባሻገር የምጣኔ ሀብት ምሰሶ የሆነውን የግብርናውን ዘርፍ ሁለንተናዊ በሆነ

> **ዋናው አሳሳቢው ጉዳይ ግን ተደጋግሞ የሚከሰትን ድርቅ በሕዝባችን ላይ የከፋ ጉዳት ሳያስከትል እንዴት መቋቋም እንችላለን የሚለውን ጥያቄ እስካሁን ድረስ መመለስ አለመቻላችን ነው። በዚህ ምክንያት በየጊዜው በርካታ ሚሊዮን ዜጎች የሚሰሩ እጆች ይዘው የተፈጥሮን ቁጣ መቋቋም አቅቷቸው እጃቸውን ለምፅዋት ሲዘረጉ እናያለን**

መልኩ ማሳደግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና፣ ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ እንደሚኖርበት ይታመናል። በተለይ 85 በመቶ የሚሆኑት ዜጎች ኑሯቸው በግብርና ላይ በተመሰረተበት ሀገር ይህ እውነታ ከፍ ያለ ትርጉም ያለው ነው።

በሀገሪቱ ጠንካራ ውጤታማ የሆነ ዘመኑን የዋጀ የግብርና ስርዓት መዘርጋት እና ለተፈፃሚነቱ መስራት ከመንግስት የሚጠበቅ ዋና ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር በግልፅ እየተሰሩ ያሉ ግብርናውን የማዘመን፣ የአስተራረስ ዘዴን የመቀየርና ምርትን ማሳደግን የተመለከቱ ተግባራት የሚበረታቱና ተስፋ ሰጭ ናቸው።

መንግስት የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን በተፈጥሮና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚከሰት ድርቅ የከፋ አደጋ ሳያስከትል አስቀድሞ ለመከላከል የሚያደርገው ጥረት ብዙ ተግዳሮቶች እያጋጠሙት እንደሆነ አይካድም። ከነዚህም ውስጥ የመንግስት ስትራቴጂክ ፖሊሲዎች በተቀናጀና በተጠናቀረ መልኩ የማስፈፀም የአመራር ክፍተት፤ ደካማ የስራ ባህል፣ ለዘመናት ሲንከባለል በመጣው ኋላቀር የአስተራረስ ዘዴ መታመን፤ ለልምድ እንጂ ለእውቀት ቅድሚያ ያለመስጠት በዋነኝነት ተጠቃሽ ናቸው።

የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ከዘመናት በፊትም ይሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ድርቅን ተከትሎ በሚከሰት ርሃብ፣ የዜጎች ሞት፣ እንግልትና ስደት ዋንኛ ምክንያት የዝናብ ወቅትን ብቻ መሰረት ያደረገው የአስተራረስ (ግብርና) ዘዴ እንደሆነ ያምናል።

በልዩ ልዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ከክረምት ወቅት ውጭ በመስኖ ግብርና አመርቂ ውጤቶች የምንመለከት ቢሆንም በጥቅሉ ግን 85 በመቶ እንደሆነ የሚገመተውን አርሶ አደር በዚህ ስርዓት ውስጥ በወጥነት ማስቀጠል አልተቻለም። ይህ ደግሞ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነው ገቢ ባሻገር በየጊዜው ዜጎችን ለከፋ ድርቅና ረሃብ እንዲጋለጡ አድርጓል።

ከድርቅ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ለድርቅ የማይበገር የግብርና ስርዓትን መገንባት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። ይህ ማለት የግብርና ዘርፉ የተትረፈረፈ ምርት ባለቤት የሚሆንበትን አቅም በጠንካራ የስራ ባህልና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መፍጠር ይገባል። ለዚህ ደግሞ መነሻ ይሆን ዘንድ የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦች ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

**ዝናብን ከመጠበቅ መላቀቅ**

ከላይ በዝርዝር ለማንሳት እንደሞከርነው የኢትዮጵያ የግብርና ስርዓት በዝናብ ውሃ ላይ የተመሰረተ /ጥገኝ የሆነ/ ነው። አሃዙ ለመለየት ተጨማሪ ጥናት ቢፈልግም 90 በመቶው አርሶ አደር ከሰማይ በሚጠብቀው ዝናብ ላይ ተመስርቶ ሞፈሩን ከመሬቱ ጋር የሚያገናኝ ነው። ይህ ደግሞ ዝናብ ሲያጥር እና ድርቅ ሲከሰት እጆቹን አጣጥፎ እንዲቀመጥ ያደርገዋል። ከራሱ ፍላጎት ያለፈ ምርት ማምረት የሚያስችል አስቻይ ሁኔታ ባለመኖሩም የምግብ ዋስትናውን አረጋግጦ ነገን በተስፋ የሚጠብቅበት እድል የለውም።

ችግሩ እየከፋ ሲሄድ በሀገር ላይ የከፋ ምጣኔ ሀብታዊ ችግር ሊያስከትል የሚችል ሲሆን ፤ ቀድሞውኑ ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን የአርሶ አደር ሕይወት ወደ ከፋ የርሃብ አደጋ በማሸጋገር ከፍ ላለ ሰብዓዊና ምጣኔ ሀብታዊ አደጋ ማጋለጡ የማይቀር ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ድርቅ በተደጋጋሚ የሚያጠቃቸው ሰቆጣና ዋግ፣ ቦረና እንዲሁም የደቡብና የምስራቁ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የምናስተውለው ችግር መነሻው ይሄው ነው። ከችግሩ ለዘለቄታው ለመላቀቅ ተፈጥሮ ጊዜ ጠብቃ ከምትለግሰን የዝናብ ውሃ ግብርናችንን ማለቀቅ ይኖርብናል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ በከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሃ ሃብት የበለፀገች ነች። በ12 ተፋሰሶች ከ122 ሚሊዮን ኪዩቢክ በላይ የገፀ ምድርና እና ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኪዩቢክ በላይ የከርሰ ምድር ውሃ ያላት ናት። ይህንን ሀብታችንን በመጠቀም አኳያ ሲታይ ያለው እውነታ ከ3 በመቶ የማይበልጥ ነው።

እንደ ሀገር ያለንን የውሀ ሀብት ወደ ልማት ብንቀይረው /በግብርናው ዘርፍ/ በድርቅ ምክንያት ከሚፈጠር የምግብ እህል እጥረት መገላገል የሚያስችለንን አቅም መገንባት እንችላለን። የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈም ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት መነቃቃት ትልቅ አቅም መፍጠር እንደሚያስችለን አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል።

ለዚህ ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግስት ስንዴን በበጋ ወቅት በክላስተር በማምረት፣ የመስኖ እርሻን በማስፋፋት እንዲሁም የከተማ ግብርናን ጨምሮ የአገሪቱን አጠቃላይ የግብርና ዘዴ በቴክኖሎጂና መካናይዜሽን ለማዘመን የሚያደረገው ጥረት እና እየተመዘገበ ያለው አበረታች ውጤት ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ኋላቀር የሆነውን የሀገሪቱን ግብርና ዘርፍ ለማዘመንና ወደሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ሳይሰለቹና ሳይታክቱ መስራት፤ ለዚህ የሚሆን የአመራር ቁርጠኝነትን መፍጠር ያስፈልጋል። የአርሶ አደር ለውጥ የሚያመጡ አዳዲስ አሰራሮችን ከባህሉና ከኢትዮጵያዊ ማንነቱ ጋር ለማስታረቅ እራሱን በስነ ልቦና ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

**የግብርናውን ዘርፍ በቴክኖሎጂ ማዘመን**

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የግብርናውን ዘርፍ በበላይነት እየመራ ያለው ቴክኖሎጂ ነው። ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ በሳይንሳዊ መንገድ ተቀምሮ ጥቂት መሬት እልፍ ምርት ይሰጣል። አንድ አርሶ አደር አንድ ቀበሌን የሚመግብበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። በአደጉት አገራት 3 ወይም 2 በመቶ የማይበልጠው አርሶ አደር ቀሪውን ዜጋ ይመግባል።

ለዚህ ታምራዊ ለሚመስል እመርታ ዋንኛ ተጠቃሹ ዓለም አሁን ላይ የደረሰችበት ቴክኖሎጂ ነው። ቴክኖሎጂው የዝናብ ወቅትን ከመጠበቅ ይልቅ የተገኘውን የውሃ አማራጭ ሁሉ መጠቀም ዓመቱን ሙሉ ምርት የሚታፈስበትን እድል ፈጥሯል።

ኢትዮጵያም የዚህ እውነታ አካል መሆን አለባት። በተለይ እያደገ ያለውን ሕዝብ ቁጥር ያለስጋት ለመመገብ ያላት ትልቁ አማራጭ ይሄው ነው። ይህንን እውን ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች ቢኖርም ከቀሪው ዓለም ጋር ሲነፃፀር ግን እያስገኘልን ያለው ውጤት የሚፈለገውን ያህል አይደለም።

በዘርፉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ሆነ ዘመናዊ የግብርና ስርአትን የሚደግፍ እና የሚያበረታታ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ቢኖረንም ወደ መሬት በማውረድ ሂደት ላይ ግን አሁንም ብዙ ችግሮች /ተግዳሮቶች/ አሉብን። ችግሮቹን ለመፍታት ከችግሮች ጋር መላመድ ሳይሆን በመፍትሄዎች ላይ ጠንክሮ መስራት ይጠበቅብናል።

እንደ ሀገር በዘርፉ ካሉብን ችግር ለመውጣት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የግዴታ መፍጠር ወይም ያልተለመዱ ሳይንሳዊ ዘዴዎችን መከተል አይጠበቅብንም። ዓለም አሁን የደረሰበትን ተሞክሮ ውጤታማ የሆኑ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ ብቻ በቂ ነው። ለዚህም ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ባለሙያዎች፣ ምሁራን እና የፈጠራ ባለሙያዎች ለግብርና ዘርፉ መሻሻል ባላቸው አቅም መስራት ይጠበቅባቸዋል።

**የአረንጓዴ አሻራን በስፋትና በጥራት ማስቀጠል**

ሌላው ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የአረንጓዴ አሻራን በስፋትና በጥራት ማስቀጠል ነው። ይህ ሀገራዊ ንቅናቄ የተመናመኑ ደኖችን መመለስና የደን ሽፋኑን መጨመር የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል የድርቅ ተጋላጭነትን ይቀንሳል።

በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት፤ የደን ሽፋንን መጨመር የከርሰ ምድር ውሃን ለማብዛት፣ የአፈር መሸርሸርና ድርቅን ለመከላከል ያግዛል። ዛፍን መትከል ሆነ ደኖችን መንከባከብ ለግብርና ዘርፍ ከሚኖረው ጠቀሜታ አንጻር እውነታውን በአግባቡ ተገንዝቦ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው።

በአጠቃላይ የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማ ለማድረግ ከዝናብ ውሃ ጥገኝነት ከመላቀቅ ጀምሮ ዘርፉን በቴክኖሎጂ ማዘመን፤ ወሳኝ ነው። ይህን ለመድረግ ደግሞ ከሁሉም በላይ በዘርፉ የሰለጠኑ ምሁራን፤ መንግስት፤ ባለድርሻ አካላትና ከራሱ ከአርሶ አደሩ ብዙ ይጠበቃል።

እስከ ዛሬ በወረቀት ላይ አስፍረን ብዙ ስንልባቸው የቆየናቸውን እነዚህን እውነታዎች መሬት አውርደን መተግበር ከቻልን፤ ለግብርናው ዘርፍ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ከመስጠታችን ባሻገር ከኋላቀርነት መርገምት እንደምንላቀቅ አንዳች እንኳን ጥርጣሬ ሊገባን አያሻም ለማለት እወዳለሁ። ሰላም!!

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

## ‹‹የፆም ዋናው አላማው የተበላሹ ማንነቶቻችንና መስተጋብሮችን መግራት ነው››

- ኡስታዝ አቡበክር አህመድ



ማህሌት አብዱል

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከምትታወቅባቸው መልካም ማንነቶች መካከል በርካታ አማኝና ለእምነቱ ተገዢ የሆነ ህዝብ ያላት መሆንዋ ነው። እነዚህ ቤተ-እምነቶች ዘመናት ያስቆጠረ የግዙፍ ታሪክና እሴት ባለቤቶች ከመሆናቸውም ባሻገር አንዱ የእምነት ተከታይ የሌላውን እምነት አክብሮ በጋራ አገርን በማቆም ረገድ ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑም ተጠቃሽ ነው። ህዝቡ በፍቅር፣ በመከባበርና በመተሳሰብ እንዲኖር በማድረግ ረገድ የእነዚህ ተቋማት ሚና የላቀ ነው። በተለይም ቅዱስ መፅሐፍትን መሰረት ያደረጉ አስተምህሮችና መመሪያዎች ህዝብን በመልካም ስነ-ምግባር በማነፅ ረገድ ድርሻቸው ከፍተኛ ነው። ከእነዚህም መካከል አፅዋማትና በወቅቱ በአማኙ የሚተገበሩት ሃይማታዊ ተግባራት ዋነኞቹ ናቸው።

በዛሬው አገርኛ አምዳችንም ዳሰሳ የሚያደርገው በትናንትናው እለት ህዝበ ሙስሊሙ አንድ ብሎ የጀመረውን 1ሺ444ኛውን የረመዳን ፆም ሲሆን በአንድ ወር ውስጥ በአማኞቹ መከናወን በሚገባቸው ሃይማኖታዊ ተግባራት ዙሪያ ነው። ለዚህም ማብራሪያ እንዲሰጡን የሃይማኖት መምህር የሆኑትን ኡስታዝ አቡበከር አህመድን አነጋግረናቸዋል፣ እንደሚከተለው ይቀርባል።

**አዲስ ዘመን፡- የረመዳን ጾም ከሌላው አፅዋማት የሚለይባቸውና ዋና ዋና ሃይማኖታዊ መርሆቹ ምን ምን እንደሆኑ ያስረዱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** በቅድሚያ ለሁሉም የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1ሺ 444ኛው ዓመት የረመዳን ጾም በሰላም አደረሳችሁ ማለት እፈልጋለሁ። ወደ ጥያቄሽ ስመለስ እንግዲህ ረመዳን በእስልምና ዘመን አቆጣጠር 12 ወራቶች ውስጥ አንደኛውና በቅዱስ ቁርዓን ጾም ግዴታ የተደረገበት ወር ነው። አላህ በቅዱስ ቁርዓን ላይ ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ከእናንተ በፊት የነበሩ ሰዎች ላይ የፆም ግዴታ እንደሆነ በእናንተም ላይ የረመዳን ፆም መፆም ግዴታ ሆነባችሁ›› ይላል። ከእስልምና መሰረታዊ መመሪያዎች ተብለው ከሚጠሩት አንዱ የረመዳንን ፆም መፆም ዋነኛው ሲሆን ማንኛው አቅም ያለው፣ ጤነኛ የሆነ ሰው፣ እድሜው የደረሰ መፆም ይገደዳል። ይህም ጎህ ከቀደደችበት ጊዜ ጀምሮ ፀሃይ እስከምትጠልቅ ድረስ የሚፈጸም የፆም ተግባር ነው። በአጠቃላይ የእምነቱ መሰረት ስለሆነ ፆም ግዴታ ነው።

የረመዳን ፆም ትልቁ አላማው የፈጣሪን ትዕዛዝ መፈፀም ነው። ፈጣሪን መፍራትና ለፈጣሪ ያለንን ታማኝነት ከምናረጋግጥባቸው መሰረታዊ አምልኮት-ስርዓቶች አንዱና ዋናው መፆም ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ፆም ከምግብና ከመጠጥ መከልከል ብቻ ሳይሆን የትኛውም ጾመኛ መላ አካሉ ከሃጥያትና ከመጥፎ ነገሮች ሁሉ መጠበቅ አለበት። ሰው ምግብ ሲከለከል በመራብ ውስጥ የሚያሳልፉ የሌሎችን ህይወት ለማስታወስ ይገደዳል። በሁለተኛ ደረጃ ለፈጣሪ ያለው ታማኝነትና ታዛዥነት በ11 ወራቶች ውስጥ የተበላሹ የአመጋገብ ስርዓትና የአኗኗር ዘይቤን ጭምር የሚስተካከል ነው። ነብያችን መሀመድ በሃዲሳቸው ‹‹ጾሙ ጤነኛ ትሆናላችሁ›› ይላሉ። ይህም አንድ ሰው ጤነኛ ለመሆን መፆም እንዳለበት ያስገነዝባል።

እናም ፆም ለፈጣሪ ያለን ታዛዥነት ውስጣችን ታማኝነት፣ ርህራሄና ይቅርባይነት የምናሳይበት ነው። በተለይ በሳለፍናቸው 11 ወራት ውስጥ በንግግራችንና በተግባራችን የተገለፁ ጥፋቶች፣ ከፈጣሪ ያፈነገጡ ተግባራት፣ የእምቢተኝነት ባህሪያት፣ በሰው ላይ ያለፍናቸው ድንበሮችና በአጠቃላይ ፆም የተበላሹብንን ነገሮች ለማስተካከልና ራሳችንን በትክክለኛ መንገድ ለማነፅና ወደ አዲስ ምዕራፍ ለመሸጋገር የሚረዳ መንፈሳዊ ማሰልጠኛ ማዕከል ነው።

አስቀድሜ እንደገለፅኩት መራብና መጠማት ባለፈ እንደአማኝ የሚጠበቅብን ነገር አለ። ነብያችንም በሃዲስ ላይ በግልፅ ይናገራሉ። ‹‹አላህ ከእናንተ መራብና መጠማት ጉዳይ የለውም›› ይላሉ። ሰው ምግብ ስለተከለከለ ብቻ ፆመ አይባልም። ፆመ የሚባለው በአካልም፣ በመንፈስም ከመጥፎ ነገሮች ሲቆጠብ በተቃራኒው መልካም ነገሮችን በመስራት ሲበረታና ሲያዘወትር ነው። ከዚያ ባሻገር ረመዳን የእዝነት ወር ነው። ይህም ማለት እርስበርስ የመተዛዘን፣ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍ ወር ነው። ነብያችን ‹‹የገሃነምን እሳት ተጠበቋት፣ በከፋይ ቴምር እንኳን›› ይላሉ። ይህም ሲባል ክፋይ ቴምር ለሰጪውም አይጎዳ፣ ለተቀባዩም አይጠቅምም፣ ግን የስጦታን ትልቅነት ነው የሚያሳየን። ትንሽ ነገር ቢኖረን እንኳን ለሎች መኖር መለማመድ አለብን። ለሌች ተስፋ መሆንና መደገፍ ይጠበቅብናል። አንዲት ጉንጭ ውሃ እንኳን ብትሆን በመስጠት፣ በማስፈጠር ከገሃነም እሳት ራሳችንን እንድንጠብቅ ነብያችን ያስተምራሉ። ይህ ወር ከመተጋገዝ፣ ከመረዳዳት ባሻገር አላህ ጋር ለመቀራረብ በጎ ተግባራትና መልካም ስራዎች የሚበረከቱበት ነው። በዚህ ጊዜ የሚሰሩ ተግባራት በ11 ወራት ከሚሰሩት ሁሉ በፈጣሪ ዘንድ እጥፍ ድርብ ዋጋ ያላቸው ናቸው። በረመዳን ውስጥ የተሰራ አንድ መልካም ስራ በሌላ ጊዜ ከሚሰራው የ70 ግዜ እጥፍ ነው በፈጣሪ ዘንድ ያለው ዋጋውና ምንዳው።

**አዲስ ዘመን፡-ከሃይማኖታዊ ግዴታው ባለፈ መረዳዳትና መደጋገፍ ኢትዮጵያዊ ባህል እንደመሆኑ በዚህ ወቅት ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** እንግዲህ የአብሮነት፣ የመተጋገዝ ባህል የኢትዮጵያውያኖች አንድ መገለጫ ነው። ረመዳን ወርም ሙስሊሙ ህብረተሰብ የእምነቱ ግዴታ የሆነውን ዘካውን (አስራቱን) የሚያወጣበት ነው። እንደሚታወቀው ማንኛውም አቅም ያለው ሰው ዘካ ይሰጣል፣ ወይም ደግሞ ሰደቃ ያወጣል። ይህንን ተግባር በረመዳን ወቅት መስጠት ይጠበቃል። በነገራችን ላይ ዘካ ሲሰጥ ዋና አላማው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የህዝብን ችግር ለመፍታት ነው። ይህም ሲባል በምፅዋት ደረጃ ዝም ብሎ መስጠት ብቻ ሳይሆን ሰዎችን እያቋቋሙ አዲስ ምዕራፍ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነው። ሰዎች ከችግርና ከተረጂነት የሚወጡበትን ስርዓት ለማበጀት ዘካ በአግባቡ እንዲሰጥ ነው እስልምና የሚያዘው። ዘካ ድህነትን ለመከላከል እስልምና እንደመፍትሔ ካቀረባቸው መከላከያ መንገዶች አንዱ ነው።

የማንኛውም ሰው ያለው ገንዘብ የአላህ ገንዘብ ነው፣ ምክንያቱም ፈቅዶ የሰጠው እሱ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ካለን ሃብት 2ነጥብ5 በመቶ የሚሆነውን ለተቸገሩ እንድንሰጥ ያዘናል። ይህም ደግሞ ለትክክለኛው ዓላማ መዋል ስላለበት ተበታትኖ ሳይሆን በተደራጀ መልኩ ለባለቤቶቹ ደርሶ ሰዎች እንዲለወጡበትና ከተረጂነት ወደ ረጂነት እንዲሸጋገሩ፣ ስራ ላይ ውጤታማ የሚሆኑበትን የማቋቋም ስራ መስራት ያስፈልጋል። በተለይም አሁን በአገራችን ላይ ከተከሰተው ድርቅ፣ ረሃብ፣ መፈናቀል፣ መሳደድ በበዛበት ወቅት ለተቸገሩ ወገኖቻችን ሰደቃ ማውጣት ከሙስሊሙ ህብረተሰብ የሚጠበቅ ነው። እነዚህ ወገኖች ትናንት ሰጪ የነበሩ ዛሬ ግን ለማኝ ሆነው ሰው ደጅ ላይ እንዲቆሙ ተገደዋል። እነዚህ ወገኖች የእኛ ወንድምና እህቶች በመሆናቸው ለእነሱ አለኝታ መከታ መሆን የበለጠ ልንረዳቸው፣ ልንደርስላቸው ይገባል።

ይህንን ማድረጋችን ደግሞ በአላህ ዘንድ የበለጠ ምንዳው ከፍ ያለ ነው። ነብያችንም በዚህ ወቅት የምስኪኖችን በር እንድንቆረቁር (እንድናኳኳ) ያዙናል። በረመዳን ወቅት ስንፆም የረሃብን ልክ የምናውቀው በመሆኑ በተፈጣሪ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የተቸገሩትን ሰዎች መደገፍ ይጠበቅብናል።

**አዲስ ዘመን፡- ቅዱስ መፅሐፍት መታዘዝንና መደጋገፍን እንደግዴታ ቢያስቀምጡም በአሁኑ ወቅት ከመደጋገፍ ይልቅ መለያየት ነው የተበራከተው። በተለይ በእምነት ተቋማት መካከልና በውስጣቸው የሚታዩት መለያየቶች እንደአገርም የሰላም እጦት ምንጭ ሆነው ይታያሉ። የዚህ ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** እንግዲህ እነዚህ መርሆዎች ፈጣሪ ለአማኞች የሰጠው ሰዎች በመልካም ስነ-ምግባር ለማነፅና ወደእሱ ፍቃድ እንዲጠጉ ለማድረግ ነው። አስቀድሜ እንዳልኩሽ የፆም ዋናው አላማው የተበላሹ ማንነቶቻችንና መስተጋብሮችን መግራት ነው። ሰዎች አካላቸው ሲደክም መልካም ማሰብ፣ ጥሩ ነገርን መፈለግ ውስጥ ይገባሉ። በመሰረቱ ሰው ሲጠግብ እኮ ነው ብዙ መጥፎ ነገሮችን ማሰብ የሚጀምረው። መድከም፣ መራብና መጠማት የበለጠ ለፈጣሪ ቅርብ እንድንሆን ያደርጋል። በሁለተኛ ደረጃ እንደአገር እየኖርንበት ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የፈጣሪያችን መመሪያዎች ግልፅና የማያሻሙ ናቸው። እስልምና ፍቅርንና ሰላምን ይሰብካል፣ የኢስላም መገለጫም ሰላም ነው። የሌላውን እምነት እንዲያከብር የእምነቱ ግዴታ ነው ግን ደግሞ በእምነት ማስገደድ አይፈቀድም። ሰዎች እኔን ካልመሰልክ ተብሎ ሊገደዱ አይገባም። ሁሉም ሰው የፈለገውን የማመን መብት የተሰጠው ከፈጣሪ ነው። ታዲያ ፈጣሪ ለእኛ ምርጫውን ሰጥቶን እያለ እኛ በሌላው ምርጫ ውስጥ ልንገባ አንችልም።

እኔ የማስተምረው ነገር ስለፍቅርና ሰላም ነው፣ ከዚያ ባለፈ ግን የእኔን እምነት ካልተከተለ ብቻ የእኔ ተቃራኒ ነው፣ የእኔ ጠላት ነው ብዬ እንዳስብ ግን አልታዘዝኩም። በተለይ በእስልምና አስተምህሮቶች ውስጥ ‹‹የመፅሐፍ ባለቤት›› እያለ በክብር ነው የሚጠራቸው። እነሱ ጋር ያለ መልካም ግኑኙነቶችን በጣም በሚያምር ቃል ነው አላህ የሚገልፀው። ‹‹እነዚያ ቀሳውስትና መነኮሳት ያላቸው ክርስቲያን ነን ያሉ ለእንናተ ለወዳጅነት ቅርብ ናቸው›› ይላል። በአጠቃላይ በመካከል ሊኖር የሚገባው ግኑኝነትና መተሳሰብ ቁርዓን በግልፅ አስቀምጦታል። አንዱ አንዱን መጥላት በእስልምና አይፈቀድም። ደግሞም እኛን የምታገናኝን የጋራ አገር አለችን። ማህበራዊ ግንኙነትና ቤተሰባዊ ትስስራችንም ጠንካራ ነው።

ከሁሉ በላይም በሰላም ተከባብረን፣ ተዋደን እንድንኖር የእምነታችን መመሪያ ነው። ቅዱስ ቁርዓን ‹‹ለጎረቤቱ የማያዝን ሰው አማኝ አይደለም›› ይላል። ጎረቤቱ ተርቦ እሱ ጠግቦ ያደረ ሰው እንዳለመነ ነው የሚቆጠረው። እዚህ ጋር ልብ ልንለው የሚገባው ጉዳይ ቁርዓን ‹‹ጎረቤት›› አለ እንጂ ሙስሊም፣ ክርስቲያን የእከሌ ዘር ብሎ አለየም። ይህ ነው የእስልምና መመሪያ። ያ ማለት ማንንም በእምነቱም ሆነ በማንነቱ ሳንለየውና ሳናገለው መልካም መመኘትና መልካም መዋል፣ ከመጥፎ ነገር መጠበቅና መከላል የእምነቱ መሰረታዊ ግዴታ ነው።

ከዚያ ውጭ ያሉ መገፋቶች የእምነት መገለጫ ወይም አካል ናቸው ብዬ አላስብም። ሰዎች እምነታቸውን ሲለቁ ስሜታቸውን ይከተላሉ። ዛሬ ‹‹የፍቅር አምላክ የሆነውን እየሱስን እከተላለው›› ያለ የክርስትና እምነት ተከታይ እንዴት ብሎ ነው ሌላውን ጠልቶና ደም አፍስሶ የእሱን ፍቅር ለማግኘት የሚችለው?። ‹‹የሰላም እምነት አለኝ›› ብሎ የሚያስብ ሙስሊም የሌላን ደም አፍስሶ፣ የሌላን ህይወት ጉዳት ላይ አጋልጦ ሊያገኝ የሚችለው ምንም አይነት የእምነት መገለጫ የሆነ ፈጣሪ ዘንድ ቅርበት አይኖረውም። እምነቱን ባለመረዳት የሚፈጠሩ ክፍተቶች ይኖራሉ፣ እምነቱ ግን ይህንን ነው የሚያዘው። በየትኛውም እምነት አማኞች ፍቅር፣ መተሳሰብ፣ ሰላምና መከባበር በማስጠበቅ አብሮ እንዲኖሩ ነው የሚገደዱት። በማይመሳሰሉበት ነገር ላይም አንዱ ለሌላው እውቅና ሰጥቶ ተከባብረው መኖር ይጠበቅባቸዋል።

ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ኢትዮጵያ የጋራ አገራችን ናት፣ አንዱ ሌላው ገፍቶ ሊኖር የሚችልባት አይደለችም፣ ይህችንን የጋራ አገር የማልማት፣ የማሳደግ፣ ሰላሟን ደህንነቷን የመጠበቅ የእያንዳንዳችን ኃላፊነት ነው። በዚህች አገር ላይ ሁላችንም ደርሻ አለን፣ ስለዚህም በጋራ ልንሰራ ግዴታችን ነው። እምነታችንም የሚያዙን ይህንን ነው። ረመዳን አንዱ ካሉት በረከቶች መካከል በሰዎች መካከል ሰላማዊ ግንኙነትንና ትስስር እንዲሁም አብሮነት እንዲጠናከር ዋነኛው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ላለው ችግር በተለይ ቤተ እምነቶችና የሃይማኖት አባቶች ትውልዱን በሚገባቸው ልክ ያለመቅረፃቸው መሆኑን ይነሳል። ይሄን እንዴት ያዩታል?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** ኢትዮጵያ ከፍተኛ የወጣት ቁጥር አላቸው ከሚባሉ አገራት አንዷ ናት። ወጣቱ የዚህች አገር ትልቁ የለውጥ ኃይል ነው። ይህችንን አገር የሚረከብ ፣ ነገ ኃላፊነቱን ወስዶ አገርን ማስቀጠል የሚችል ማንነት አለው። እርግጥ ነው፣ ወጣቱ መጠቀሚያ ሊሆን የሚችልበት እድሎች አሉት። በተለያየ መልኩ ወጣቱን ለጥፋትና ለመጥፎ ዓላማ ሊጋብዙ የሚችሉ ስራዎች ይሰራሉ። ዛሬ ጥፋትም የሚያጠፋው፣ አገርም የሚያለማው ሁሉም ይፈልገዋል። ይህ ወጣት ደግሞ የበለጠ ትክክለኛውን መስመር ተከትሎ እንዲኖር፣ የተፈጠረበትን ዓላማ ሳይዘነጋ ባለው አቅም ለመልካም ነገር እንዲጠቀም ለማድረግ እንዲሁም የሰብአና ከፍታ ላይ እንዲቀመጥ ቤተ-እምነቶች ትልቅ ድርሻ አላቸው። በስነ-ምግባር የማነፅና የመቅረፅ ኃላፊነት የቤተ-እምነቶችና የሃይማኖት አባቶች ድርሻ ነው። ዛሬ እየከፈልን ያለነው ዋጋ ትናንት ባልሰራነው የቤት ስራ ምክንያት ነው። ስራችንን በአግባቡ መስራት ባለመቻላችን ነው አማኝ የሆነ ማህበረሰብ አለ በሚባልባት አገር ላይ የሚፈፀመው ግፍ ማሰብ ከሚቻለው በላይ ከባድ የሆነው። ትውልዱ ላይ ምን ሰራን? ብለን ልንጠይቅ ይገባል። ዛሬ አገር የሚያምሰው፣ አገር የሚያጠፋው፣ በማህበራዊ ሚዲያው ጠብንና ጠላትነትን እንዲሁም እርስበርስ መበላላትን የሚሰብከው ወጣት የእኛው ስሪት ውጤት ነው። ከየትም አላመጣነውም፣ በእምነቱም ቢሆን ይህንን ወጣት ክርስቲያን ወይም ሙስሊም የሌላ ቤተ-እምነት ተከታይ መሆኑ አይቀርም። ይህ አካል ይህችው ምድር ያበቀለችው፣ በእኛው ቤት ውስጥ ያደገ፣ በእኛ እጅ የተገነባ ነው። ስለዚህ ምንአይነት ስራ ሰርተን ነው ይሄ ትውልድ በዚህ ደረጃ የወረደው? ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ኡስታዝ አቡበከር፡- እኔም አመሰግናለሁ።**

# ወጣቶች

# ሥራ ፈጠራ ስምሩቃን ተማሪዎች

**አስናቀ ፀጋዬ**



ወጣት ሻላም እዮብ በሃዋሳ ዙሪያ ሮኬሰ ሱኬ ቀበሌ ነው ተወልዶ ያደገው። እንደብዙዎቹ የሃዋሳ ዙሪያ ወጣቶች እርሱም የግብርና ስራን ከቤተሰቦቹ ተምሯል። በግብርና ብቻ ሳይሆን በቀለም ትምህርቱም ገፍቶ ከአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ በአካውንቲንግ በ2012 ዓ.ም በዲግሪ ተመርቋል። እስከ 2014 ዓ.ም ድረስም በለስ ሳይቀናው ቀርቶ ስራ ሳይዝ ቆይቷል።

ሆኖም የሲዳማ ክልል የስራ፣ ክህሎትና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በ2014 ዓ.ም ወጣቶችን አደራጅቶ ወደስራ ከማስገባቱ በፊት በአስተሳሰብ ለውጥ ዙሪያ ስልጠናዎችን ሲሰጥ እርሱም ተካፍሎ የሚፈልገውን እውቀት ቀስሟል። ልክ እንደእርሱ ሁሉ እርሱ በተመረቀበት ዓመት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ወጣቶችም ስልጠናውን ተከታትለዋል።

ከስልጠናው በኋላ እርሱን ጨምሮ 19 ወጣቶች ሆነው በሶስት ማህበራት በመደራጀት በግብርና ዘርፍ ስራ ጀምረዋል። የግብርና ስራውን የጀመሩትም አብዛኞቹ ወጣቶች በሚኖሩበት ሮኬሰ ሱኬ ቀበሌ በሚገኝ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በኪራይ በቀረበላቸው መሬት ላይ በቆሎ በማምረት ነበር። በዚሁ ዓመትም በቆሎ አምርተው እሸቱን ለገበያ አቅርበው 800 ሺ ብር ማግኘት ችለዋል።

በዚሁ ዓመትም በተመሳሳይ በቆሎ በማምረት 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት አቅደው እየተንቀሳቀሱ ሲሆን የማሳ ዝግጅት አድርገዋል፤ ከክልሉ ግብርና ቢሮ የበቆሎ ዘር ለመውሰድም ተዘጋጅተዋል። ከበቆሎው በኋላም ቦሎቄ ወይም ድንች የመዝራት ሃሳብ አላቸው።

«ትምህርቴን አጠናቅቄ ስራ ለማግኘት ብዙ ተቸግሬ ነበር» የሚለው ወጣት ሻላም፤ በማህበር ተደራጅቶ በግብርና ዘርፍ መስራት ከጀመረ ወዲህ የተሻለ ገቢ እያገኘ እንደሚገኝና ለቀጣይ ህይወቱ ጥሩ መሰረት እየጣለ እንደሚገኝ ይገልፃል። በተለይ ደግሞ ግብርና ስራ ብዙም ውጤታማ አያደርግም የሚል አስተሳሰብ እንደነበረውና ገብቶ ሲሰራበት ግን የተሻለ ገቢ የሚያስገኝና ህይወት ሊለውጥ የሚችል መሆኑን እንደተረዳም ነው የሚናገረው።

በተመሳሳይ ተመርቀው ያለስራ የተቀመጡ ሌሎች የክልሉ ወጣቶችም በማህበር ተደራጅተው ስራ ሳይንቁ ቢሰሩ ከራሳቸው አልፈው ቤተሰባ ቸውን፣ አካባቢያቸውንና ክልላቸውን ሊለውጡ እንደሚችሉ ይጠቁማል። ሁሉም ወጣቶች ተቀጥሮ ከመስራት ይልቅ በማህበር ተደራጅቶ የመስራትን ባህል ሊያዳብሩ እንደሚገባም በዚሁ አጋጣሚ ይመክራል።

ወጣት ሳሙኤል ዘለቀም በ2013 ዓ.ም በፐብሊክ አድሚንስትሬሽን የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። በ2015 ዓ.ም በአስተሳሰብ ለውጥ ዙሪያ የክልሉ የስራ፣ ክህሎትና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የሰጠውን ሥልጠና ወስዶ ከሌሎች 26 ተመራቂ ተማሪዎች ጋር በግብርና ዘርፍ በማህበር ተደራጅቶ ስራ ጀምሯል።

በተደራጁበት በዚሁ የ2015 ዓ.ም ዘመንም በአርቤጎና ወረዳ ሆሰና ሜቶ ቀበሌ ገብስ ዘርተው ምርት እየሰበሰቡ ይገኛሉ። እስካሁንም ስልሳ ሶስት ኩንታል ገብስ መሰብሰብ ችለዋል። ቀሪውን 10 ኩንታል የመሰብሰብ ስራ እየሰሩ ነው። በሄክታር 200 ኩንታል ገብስ ለመሰብሰብና በአንድ ኩንታል 336 ሺ ብር ገቢ ለማግኘት እቅድ የነበራቸው ቢሆንም መሬቱን ለማከም ኖራ ባለማግኘታቸው የሚጠበቀውን ምርት ሊያገኙ እንዳልቻሉ ይናገራል ወጣት ሳሙኤል።

ሆኖም ነገሮች ከተስተካከሉ በቀጣይ የተሻለ የገብስ ምርት በማምረትና ለገበያ በማቅረብ ገቢያቸውን ለማሳደግ ብሎም ሌሎች ምርቶችንም በማምረት ተጠቃሚ ለመሆን እየሰሩ እንደሚገኙም ይገልፃል። በማህበር ተደራጅቶ በመስራቱ ደስተኛ መሆኑንና በቀጣይ እርሱና የማህበሩ አባላት ጠንክረው ከሰሩ የተሻለ ምርት የማግኘት እድል እንዳላቸው ይጠቁማል።

አቶ ከፍያለው ከበደ የሲዳማ ክልል ስራ፣ ክህሎትና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት በ2015 ዓ.ም 58 ሺ 146 ለሚሆኑ በክልሉ ለሚገኙ ወጣቶች ቋሚ የስራ እድል ለመፍጠርና 50 ሺ ለሚሆኑት ነባር ኢንተርፕራይዞች የተለያዩ ድጋፎችን ለማድረግ እቅድ ተይዞ ወደስራ ተገብቷል።

በዚሁ እቅድ መሰረት እስከ ሰባተኛው ወር መገባደጃ ድረስ 32 ሺ 262 ለሚሆኑ ወጣቶች በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ ቋሚ የስራ እድል መፍጠር ተችሏል። በእያንዳንዱ ዘርፎች በተናጠል ሲታይም በግብርና 6 ሺ 900፣ በኢንዱስትሪ 10ሺ238 እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፍ 15 ሺ 124 የስራ እድል ለወጣቶቹ ተፈጥሯል።

በግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ በተለየ መልኩ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ሲሆን በዋናነት በገጠራማው ክፍል የትምህርት ቤት መሬቶችን ጭምር ለወጣቶች በማቅረብና አስፈላጊውን ግብአትና ስለጠናዎች እንዲያገኙ በማድረግ በግብርናው ዘርፍ እንዲሰማሩ ተደርጓል። በኢንዱስትሪ ዘርፍ በተለይ በተፈጥሮና በኢንዱስትሪ ማእድናት እንዲሁም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍም በርካታ የስራ እድሎች ተፈጥረዋል።

መንግስት ለግብርናው ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደመሆኑና የሌማት ትሩፋትም ከዚሁ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ክልሉ ደግሞ ገበያ ተኮር ሰብሎች አብቃይና የበርካታ ተፈጥሯዊና የኢንዱስትሪ ማእድናት መገኛ ስለሆነም ጭምር የወጣቶች የስራ እድል ፈጠራው ይበልጥ በግብርናና በኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩር መደረጉን ኃላፊው ያስረዳሉ።

እንደ አቶ ከፍያለው ገለፃ ቢሮው ካስቀመጠው እቅድ አኳያ አፈፃፀሙ ሲታይ የዓመቱን 69 ከመቶ ያህሉን ማሳካት ችሏል። ከሰባት ወሩ አንፃር ሲታይም ወደ 89 ከመቶ ያህሉን መፈፀም ተችሏል። በተለየ መልኩ ቋሚ የስራ እድል ላይ ትኩረት መሰጠቱ እንዲሁም ግዚያዊውን ደግፎ ወደቋሚ የማምጣት ስራ በመሰራቱ ብሎም ለምሩቃን ተማሪዎች የተለየ ትኩረት መሰጠቱ የስራ እድል ፈጠራውን ለየት ያደርገዋል። በተለይ በዲግሪና በዲፕሎማ ከተለያዩ የትምህርት ተቋማትና የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ማእከላት ለተመረቁ ተማሪዎች በተለየ መልኩ ትኩረት ተደርጎ ተሰርቷል።

በዚሁ መሰረት 4 ሺ 200 ለሚሆኑ በዲግሪ፣ 10ሺ981 ለሚሆኑ በዲፕሎማ እና 17 ሺ 81 በሰርተፍኬት ለተመረቁና አስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍል ላጠናቀቁ ተማሪዎች ቋሚ የስራ እድል ተፈጥሯል። ለተቀሩት ወጣቶች ደግሞ በግዚያዊነት ስራ በመፍጠርና በመደገፍ ቋሚ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል። በገጠሩ አካባቢ ደግሞ በየወረዳው ያሉ ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም በግብርናው መስክ የራሳቸውን ስራ ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ ያሉ ወጣቶችም አሉ።

ክልሉ ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት የለውጡን መነሻ ተከትሎ በርካታ ስራ አጥ ወጣቶች የሚገኙበት እንደመሆኑ ይበልጥ ምሩቃን ተማሪዎች ላይ ትክሩት ተደርጎ የማይሰራ ከሆነ ጉዳዩ ይበልጥ አሳሳቢ እንደሚሆን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል። በየደረጃው ያሉ አካላትም ከተመረቁ ተማሪዎች በታች ባሉት ወጣቶች ላይም በማተኮር የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል።

ይህ በመደረጉም በክልሉ ያለውን የስራ አጥ ምጣኔ በ2013/14 ዓ.ም በገጠርና በከተማ ከነበረበት 17 ነጥብ 4 ከመቶ በ2015 ዓ.ም ወደ 13 ነጥብ 9 በመቶ ማውረድ ተችሏል። አገር ላይ ካለው የስራ አጥነት ምጣኔ አንፃርም ሲታይ የክልሉ የስራ እድል ፈጠራ ሂደት ፈጣን መሆኑን ያሳያል።

አቶ ከፍያለው እንደሚሉት ለወጣቶቹ የስራ እድል ለመፍጠር በቅድሚያ ልየታ ተደርጎ በአስተሳሰብ ለውጥ ዙሪያ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በዚህም በአብዛኛው ተመራቂ ወጣቶች ዘንድ የነበረውን በመንግስት ተቋማት ውስጥ ተቀጥሬ እሰራለሁ የሚለውን አስተሳሰብ መቀየር ተችሏል።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም የክልሉ የሲዳማ ክልል ስራ፣ ክህሎትና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ባለፈው በጀት ዓመት 8 ሺ 900 ለሚሆኑ ወጣቶች የአስተሳሰብ ለውጥ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። እነዚህ ሰልጣኝ ወጣቶች የራሳችንን ስራ ፈጥረን የምንሰራ ከሆነ ከራሳችን አልፈን ለሌላም መትረፍ እንችላለን የሚለውን አላማ መሰነቅ ችለዋል።

ቢሮውም ወጣቶቹ የሚሰማሩባቸውን ማዕቀፎችን እንደገና የመከለስ ስራ ሰርቷል። በየአካባቢው ያሉ ፀጋዎችና ምቹ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ፣ የትኞቹ አካባቢዎች ላይ ወጣቶቹ ቢሰማሩ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ በመለየት ወደስራ ተገብቷል። ለአብነትም በሃዋሳ ከተማና ዙሪያ ላይ በኮንስትራክሽን በተለይ ደግሞ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ወጣቶቹ ቢሰማሩ በአጭር ግዜ ውጤታማ ሆነው ለሌሎች ስራ ወጣቶችም በግልም ሆነ በግዚያዊነት በሚሰጡት የስራ እድል መፍጠር እንደሚችሉ ተረጋግጦ በዚሁ ዘርፍ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

በሌላ በኩል ደግሞ ለዶሮ ልማት፣ ለወተትና ለከብት ማደለብ የትኞቹ ወረዳዎች ምቹ እንደሆኑ ቀድሞ በመለየት ወደ 41 የሚሆኑ የስራ እድል መፍጠሪያ ማዕቀፎች አሁን ያለውን የገበያ ሁኔታና በየአካባቢው ያለውን እምቅ አቅም ታሳቢ በማድረግ የክለሳና ተጨማሪ ፓኬጆች እንዲጠኑ በማድረግ ለወጣቶቹ የስራ እድል ተፈጥሯል። ምሩቃን ተማሪዎችም ከግዜ ወደ ግዜ የመንግስትን ስራ ከመፈለግ ይልቅ የራሳቸውን ስራ እንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

ለአብነትም በሃዋሳ ዙሪያ ባሉ ወረዳዎች በበቆሎ ሰብል አምና ቁጥራቸው በርከት ያሉና ወደ 380 የሚሆኑ በዲግሪ የተመረቁ ተማሪዎች ተሰማርተው የላቀ ውጤት ማምጣት ችለዋል። እነዚህ ወጣቶችም በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የመስራትን አስተሳሰብ ትተው ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ስራ ላይ አተኩረዋል። በሰፋፊ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ያሉ መሬቶችን ተከራይተው ገብስና ስንዴ በማምረትም ጥሩ ውጤት እያስመዘገቡ መጥተዋል።

በካፒታል የሚሰሩ ፕሮጀክቶችም ለወጣቶች ብቻ እንዲሰጡ በመደረጉ የሚጠገኑና አዳዲስ መንገዶችን በዚሁ ዘርፍ የተደራጁ ወጣቶች እንዲሰሯቸው ተደርጓል። በ2013/14 በጀት ዓመት 3 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት ችለዋል። በዚሁ ዓመትም የተሻሉ ኢንተርፕራይዞች ተመልምለው ከ 2 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እንዲገኙ ተደርገዋል። በሀዋሳ ከተማ አምና ከ1 ሺ 200 በላይ የሚሆኑ በዲግሪ የተመረቁ ወጣቶች በኮብል ስቶን ንጣፍ ስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

አቶ ከፍያለው እንደሚናገሩት ከመንግስታዊ ድጋፎች ውስጥ ብድር፣ ቁጠባ፣ መሬትና ሼድ አቅርቦት ይገኙበታል። በዚህ ዓመት 556 ሄክታር መሬት ለወጣቶች ለማቅረብ ታቅዶ እስከ ሰባተኛው ወር መገባደጃ ድረስ 326 ሄክታሩን ማቅረብ ተችሏል። ይህም ከዚህ በፊት ቀድመው የተሰጡ መሬቶች እንዲመለሱ በማድረግ አሁን እንደገና ለወጣቶቹ የተሰጣቸውን ሳይጨምር በአዲስ መልክ ለወጣቶች እንዲሰጥ የተደረገ መሬት ነው። አምና በተመሳሳይ ወቅት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

ብድር አቅርቦትን በሚመለከት ክልሉ በዚህ ዓመት ለወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ 100 ሚሊዮን ብር መድቧል። ከዚህ ውስጥ በመጀመሪያው ዙር 30 ሚሊዮን ብር ለወጣቶቹ ተላልፎ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። ከብድር የሚመለሰው ገንዘብም በድጋሚ ለአዳዲስ ስራ ፈጠራ እንዲውል ለወጣቶቹ ተሰጥቷል። 198 ሚሊዮን ብር ብድር ለማስመለስ ታቅዶም እስከ ሰባተኛ ወር ድረስ 75 ሚሊዮን ብር ያህሉን ማስመለስ ተችሏል። ከእቅዱ አንፃር ግን በቀጣይ ቢሮው ብዙ ነገር መስራት እንዳለበት ይጠቁማል። እንዲያም ሆኖ ግን ከፌደራል መንግስት የተመደበውን ጨምሮ እስከ ሰባተኛ ወር ድረስ 82 ሚሊዮን ብር ለወጣቶቹ የብድር ስርጭት ተደርጓል።

ወጣቶች ወደስራ ከተሰማሩ በኋላና ተሰማርተው ያገኙትን ውጤት መነሻ በማድረግ ገንዘብ እንዲቆጥቡ ተደርጓል። በዚሁ በጀት ዓመትም 89 ሚሊዮን ብር ለማስቆጠብ እቅድ ተይዞ እስከ ሰባተኛ ወር ድረስ 73 ሚሊዮን ብር ማስቆጠብ ተችሏል። ይህም ወጣቶቹ በተሰማሩበት ስራ ውጤታማ መሆናቸውን ያሳያል። ከስልጠና ጋር በተያያዘም 39 ሺ የሚሆኑ ወጣቶችን ለማሰልጠን ታቅዶ እስከ ሰባተኛ ወር ድረስ 19 ሺ 300 ወጣቶችን ስልጠና በመስጠት ወደስራ ማሰማራት ተችሏል። ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲታይ የተሻለ ነው።

ክልሉ በዚህ ደረጃ ለወጣቶች የስራ እድል በመፍጠር ከስራ አጥነት እያላቀቀ ቢሆንም አሁን ካለው የስራ አጥነት ምጣኔ አንፃር ገና ብዙ መሰራት ያስፈልጋል። ለዚህም ነው ስራ አጥነት ላይ የተለየ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ያለው። በተለይ በተመራቂ ተማሪዎች ላይ እየተሰራ ያለው ስራ በወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ መሬት ላይ በትክክል እየተሰራ ያለውን ስራ ይጠቁማል።

# የምድር በረከት

## ‹‹ኢንስቲትዩቱ አሁን ትኩረት ቢሰጠውም፣ ለበለጠ ውጤታማነት በቴክኖሎጂ መታገዝ አለበት››

*- ዶክተር ደጀኔ ኃይለማርያም*
*የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር*

ሰምሰም መንግሥቱ

**የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት የሥነምድር ካርታ ሥራን ጨምሮ በጥናትና ምርምር የሥነምድር መረጃዎችን በስፋትና በጥራት በማጥናት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ ተልዕኮ ይዞ ሲሰራ ቆይቷል። ኢንስቲትዩቱ የማእድን አለኝታና ክምችት ጥናት በማካሄድ ይታወቃል፣ በስነምድር ሳይ ለመንግስታዊና መንግስታዊ ሳልሆኑ ተቋማትም የምክር አገልግሎት ይሰጣል። በአሁኑ ወቅት ተልዕኮውን የበለጠ ለመወጣት የሚያስችለውን አደረጃጀት አግኝቷል።**

**ኢንስቲትዩቱ እያከናወናቸው ስለሚገኙ ተግባሮች፣ በአዲስ መልክ መደራጀቱ ስላስው ፋይዳና ሴሎች ተያያዥ ጉዳዮች ከኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ደጀኔ ኃይለማርያም ጋር ያደረግነውን ቃስ ምልልስ በዛሬው የምድር በረከት አምዳችን ይዘን ቀርበናል።**

**አዲስዘመን፡- በቅድሚያ ኢንስቲትዩቱ ስለሚሰጣቸው የሥነምድር መረጃዎችና ስለ አዲሱ አደረጃጀቱ ቢገልጹልን?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** ኢንስቲትዩቱ እንደ መንገድ ላለ መሠረተ ልማት እንዲሁም የህንፃ ግንባታ ከመከናወኑ በፊት በሚያስፈልጉ መረጃዎች ላይ በጥናት የተደገፈ የሥነምድር መረጃ ይሰጣል። መረጃውን ዩኒቨርሲቲዎች ለጥናት መነሻ እንዲጠቀሙበት ምቹ ሁኔታም ይፈጥራል።

መሠረታዊ የጂኦሎጂ ወይንም የሥነምድር ካርታ ያጠናል። በዚህም የሥነምድር አለኝታ ቦታን ይለያል። በዚህ የሥነምድር ካርታ ጥናቱም ማዕድን የሚገኝበትን ሥፍራ ያመላክታል፤ ይህ ብቻ ሳይሆን ክምችቱንም ጭምር የሚያሳይ መረጃ ለይቶና ከልሎ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ያደርጋል። በዚህ መረጃ ውስጥም መሬት ውስጥ ያለ የጂኦተርማል ወይንም የእንፋሎትና የነዳጅ ዘይት፣ የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ካርታና የጥናት ሪፖርት ዝግጅት ይገኝበታል። የሥነምድር ጥናት ምርምርን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ የቁፋሮ፣ የቤተሙከራ (ላብራቶሪ) እና የምክር አገልግሎቶችን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት በመስጠትም ኢንስቲትዩቱ ይሰራል።

ኢንስቲትዩቱ ላለፉት 55 ዓመታት በዚህ መልኩ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም፣ አሁን ከሚሰራው በላይ አቅም ፈጥሮ ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ በማድረግ ረገድ የሚያገኘው ድጋፍ አናሳ ነበር። በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ መረሳት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ማለት ይቻላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ኢንስቲትዩቱ የበለጠ ተልዕኮውን እንዲወጣ የሚያስችለው አደረጃጀት ተፈጥሯል። ይህም መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ያመለክታል። አሁን ባለው አደረጃጀት መሠረት ኢንስቲትዩቱ በጥናት ያደራጀውን መረጃ ለማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ይሰጣል። ይህ ክፍል ደግሞ የአዋጭነት ጥናት ያካሂዳል።

ማዕድኑ በምን ቴክኖሎጂ ሊለማ እንደሚችል ጭምር በጥናቱ አካቶ ለማዕድን ሚኒስቴር ይሰጣል። ማዕድን ሚኒስቴር ደግሞ በዚህ ሂደት ማለፉን ካረጋገጠ በኋላ ለአልሚዎች ፈቃድ በመሥጠት ልማቱ እንዲከናወን ያደርጋል። እንዲህ አይነት የተናበበ አሰራር ቀደም ሲል አልነበረም። በአዲሱ አደረጃጀት ሥራዎች በዚህ መልኩ ነው የሚከናወኑት።

በሰው ኃይል በኩልም ቀደም ሲል ኢንስቲትዩቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተርና ዋና ጂኦሎጂስት ነበር የሚመራው። በአሁኑ አደረጃጀት ግን በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በሶስት ሥራ አስፈጻሚዎች እንዲመራ ተደርጓል።

አንዱ የማዕድን ሀብት ሥራ አስፈፃሚ ሲሆን፣ በሥሩ የማዕድን ፍለጋ ምርምር፣ የጂኦተርማል ሀብት ምርምር እንዲሁም የድሪሊንግ አገልግሎትና የጂኦፊዚክስ ምርምር ዴስክ ወይንም ክፍሎች ይገኛሉ። በሁለተኛው ሥራ አስፈጻሚ ሥር ደግሞ የጂኦሣይንስ ካርታ ሥራ፣ ምርምር፣ የሥነምድር አደጋዎችና ጂኦቴክኒክ ምርምር፣ የጂኦሳይንስ መረጃና የጂኦኬሚስትሪ ምርምር ዴስኮች ወይንም ክፍሎች አሉት። ሶስተኛው የጂኦሳይንስ ላብራቶሪ ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን፣ በሥሩም የጂኦኬሚካል፣ የሚኖሮሎጂና የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ጥገና ይገኛሉ።

በአዲሱ አደረጃጀት አገልግሎቶችን የጋራ በማድረግ ለሥራ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ተደረገ እንጂ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለማዕድን ሚኒስቴር ቢሆንም፣ በራሱ በጀት ነው የሚተዳደረው። አደረጃጀቱ ሥራን የሚያቀላጥፍ እና የማያቀላጥፍ መሆኑ እየተፈተሸ ለአሰራር ምቹ የሆነ ነገር እንዲፈጠር ይደረጋል።


ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ በእስካሁኑ እንቅስቃሴው ምን ተልእኮዎችን ተወጥቻለሁ ይላል?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** ኢንስቲትዩቱ ባለው የሰው ኃይል፣ በጀትና አደረጃጀት የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚችለውን ሲያደርግ ቆይቷል። ከእነዚህ መካከልም በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የብረት ምርት/ጥሬ እቃ/ በአገር ውስጥ ለመተካት በመንግሥት የተያዘውን አቅጣጫ ለማሳካት እያደረገ ያለው ጥረት ይጠቀሳል።

ኢንስቲትዩቱ በዚህ በኩል እየተወጣ ባለው ድርሻ ባደረገው የጥናት ሥራ በሰቆጣ፣ ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ መካነሰላም በሚባሉ አካባቢዎች የብረት ማዕድን ልየታ ሥራ አከናውኗል። ክምችቱን በጥናት የመለየት ሥራ ከተከናወነ በኋላ ደግሞ ክምችቱን ለማረጋገጥ ወደ ሁለተኛው ምእራፍ የቁፋሮ ሥራ መሸጋገር ተችሏል። የቁፋሮው ሥራውም ልየታ በተደረገበት ጉጂ ላይ ነው ለጊዜው የሚከናወነው።

ኢንስቲትዩቱ በልየታ ላይ ነው ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ የነበረው። የለየውንም ቁፋሮውን ለሚያከናውን አካል ወይንም ኩባንያ ነበር አሳልፎ የሚሰጠው። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ምን ያህል ክምችት አለው የሚለው በኢንስቲትዩቱ እንዲረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ለጊዜው በብረት ማዕድን ላይ ቁፋሮ እንዲጀመር ተደርጓል።

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ለኃይል ግብአት በሚውል የድንጋይ ከሰል ላይም በተመሳሳይ በተከናወነው ሥራ ጅማ፣ ደቡብ ምእራብ፣ ቤኒሻንጉልጉሙዝ ልየታ ማድረግ ተችሏል። በወርቅ ማዕድን ዙሪያም እንዲሁ ኢንስቲትዩቱ በየጊዜው የጥናት ሥራ ያከናወናል። ባለፈው ዓመት በሲዳማ ክልል ላይ ጥናት ተደርጓል።

የጥናት ውጤቱም ለየክልሎቹ የማድረስ ሥራ ይሰራል። በጥናት የተደራጀ መረጃ አልሚ ሲመጣ ጥናቱን መሰረት አድርጎ እንዲያለማ ከማስቻሉ በተጨማሪ ክክሎችም ሥራ ያቀልላቸዋል። በደቡብ ክልል አካባቢም በጌጣጌጥ ማዕድን ላይ የጥናት ሥራ ተሰርቷል።

**አዲስ ዘመን፡- የቁፋሮ ሥራው ለጊዜው በብረት ማዕድን ላይ ነው የሚከናወነው። በወርቅና ሌሎቹ የማዕድን አይነቶች ላይ በተመሳሳይ ቀጣይ ተግባር ይኖራል?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** የወርቅ ማዕድንን በተመለከተ በጥናት የቦታ ልየታው ይካሄዳል፤ የማዕድን ክምችት ግን በግምት ነው መረጃው የሚጠናቀረው። ግምቱ ግን ለእውነት የተጠጋ ነው። ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደረጃ ያለውንና ያረጋገጠውን መረጃ ለሚመለከተው አካል ይሰጣል።

እስካሁን ባለው አሰራርም ለኩባንያ ነው አሳልፎ የሚሰጠው። የወርቅ ቁፋሮ ሥራ አስር ዓመትና ከዚያም በላይ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ኢንስቲትዩቱ አለኝታ ቦታን ለይቶ መሥጠቱ በራሱ ከፍተኛ መረጃ ነው። ኩባንያዎችም ሆኑ በአነስተኛ ተደራጅተው በዘርፉ የሚሰሩ መረጃውን ካገኙ አስፍተው ለመቀጠል ዕድል ይሰጣቸዋል።

የጌጣጌጥ ማዕድን ዘርፍ ግን ለየት ይላል፤ ማዕድኑ በቀላሉ አይገኝም። ቦታውን በራሱ መለየት አንድ ነገር ነው። ክምችቱን ማወቅ ያስቸግራል። እስካሁን ባለው አሰራር አካባቢውን በማመላከት ሥራ ላይ ነው ትኩረት የተደረገው።

የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ላይ ኢንስቲትዩቱ ጥናት እንዲያካሂድ ተልእኮ ቢሰጠውም ሥራውን ግን አልሄደበትም። በዘርፉ ኩባንያዎች ናቸው እየተንቀሳቀሱ ያሉት። ዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ ከፍተኛ መዋእለነዋይና ቴክኖሎጂ ይጠይቃል። ኢንስቲትዩቱ በዚህ ደረጃ የተደራጀ ባለመሆኑ ነው ወደ ሥራ ያልገባው። ሆኖም ግን በኢትዮጵያ ከኦጋዴን አካባቢ በተጨማሪ በስምጥ ሸለቆና በሌሎችም የአገሪቱ አካባቢዎች የሀብት ክምችቱ አለ።

ለግንባታው ዘርፍ ግብአት በሚውሉ የማዕድን ዘርፎች ላይም ኢንስቲትዩቱ ጥናት ያካሂዳል። በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ በአምስት አካባቢዎች ላይ ግራናይት መኖሩን የሚያረጋግጥ መረጃ ለክልሉ ሰጥቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ የማዕድን ሀብትን እንደየዘረፉ በመለየት ተደራሽ ያደርጋል። ሀብቱ መኖሩን ከማረጋገጥ ባለፈ ጥቅም ላይ ውሎ በምጣኔ ሀብቱ ላይ አስተዋጽኦ ሲያበረክትና ማህበረሰቡም ከልማቱ ተጠቃሚ ሲሆን ማየት ነው የመጨረሻው ግብ። በመሆኑም ውጤቱስ ለሚሉ ምላሽዎ ምንድነው? በእያንዳንዱ የማዕድን ዘርፍ ያለው የክምችት መጠንስ ምን ያህል ይታወቃል?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** ኢትዮጵያ በአጠቃላይ ካላት እምቅ የከርሰምድር ሀብት ለይተናል ብለን መናገር የምንችለው ከ20 በመቶ አይበልጥም። ከዚህ በላይ ላለመሄዳችን ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው። የትኩረት ማነስ እንደ አንድ ምክንያት ይወሰዳል። ኢንስቲትዩቱ በሙሉ አቅሙ ይንቀሳቀስ ነበረ ለማለት አያስደፍርም።

ይህ ተቋም የማዕድን ሚኒስቴር የጀርባ አጥንት ነው ማለት ይቻላል። አሁን ላይ የተሻለ ትኩረት ቢያገኝም፣ ብዙ ለመሥራትና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በቴክኖሎጂ መታገዝ አለበት። ያደጉ አገሮች የማዕድን ልየታ ጥናት ሥራን በአውሮፕላን በመታገዝ ጭምር ነው የሚሰሩት።

**አዲስ ዘመን፡- በዘርፉ ገና ብዙ ሥራ የሚጠበቅ ከሆነ፣ ኢትዮጵያ እምቅ ሀብት አላት የሚባለው ምንን መሰረት በማድረግ ነው?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** በባህላዊ የአሰራር ዘዴም ሆነ አነስተኛ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተሰሩት ሥራዎች እንዲሁም በዘርፉ ላይ ተሰማርተው ከሚንቀሳቀሱና በተለያየ መንገድ ከተገኘ መረጃ መረዳት የሚቻለው ኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያላት መሆኑን ነው።

**አዲስዘመንስ፡- ኢንስቲትዩቱ በተጠናከረ አደረጃጀት ውስጥ ባልነበረበት ወቅትም ሆነ አሁን በአዲስ መነቃቃት ባደረገው እንቅስቃሴ ፈተናዎች እንደሚያጋጥሙት ይታወቃልና ፈተናዎቹ ምንድናቸው? እንዴትስ እያለፋቸው ነው?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** የሰለጠነ ባለሙያ ፍልሰት አንዱ የዘርፉ ተግዳሮት ነው። የተሻለ አሰራር ያለው ኩባንያና ክፍያ ፍለጋ ብዙ የዘርፉ ባለሙያዎች ስራ ትተው ይሄዳሉ። ዘርፉ አሁን ላይ በአዲስ አደረጃጀት መዋቀሩን ተከትሎ ባለሙያዎችን ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው። ለእዚህም ዩኒቨርሲቲዎች የዘርፉን ባለሙያ እንዲያፈሩ በጋራ እየተሰራ ይገኛል። በራስ አቅም በማሰልጠን ክፍተቱን ለመሙላትም ጥረት እየተደረገ ነው።

ሌላው የኢንስቲትዩቱ የጥናት ሥራ በቤተሙከራ መደገፍ ይኖርበታል። ይሁን እንጂ ቤተሙከራው በቆየ አደረጃጀት ውስጥ ነው ያለው። የሚጠበቅበትን መውጣት እንዲችል ለምርምር አጋዥ ነገሮች ሊሟሉለት ይገባል።

ቤተሙከራው የቤተሙከራ ፍተሻ እንዲደረግላቸው የሚፈልጉ አካላትን ጨምሮ የፍተሻ አገልግሎት ለሚፈልጉ ሁሉ በክፍያ አገልግሎት ይሰጣል። የክፍያ አገልግሎቱ አሁን ካለው ወቅታዊ ገበያ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ባለመገኘቱ አገልግሎት ሰጥቶ የሚያገኘው ገቢ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር አይደለም። ክፍተቶች ቢኖሩም፣ ባለው ለመጠቀም ጥረት እየተደረገ ነው።

በዚህ ብቻ ውጤታማ መሆን ስለማይቻል ቤተሙከራውን ማዘመን ግዴታ ነው። ለእዚህም ጥረቶች ተጀምረዋል። ከአንድ የካናዳ ድርጅት እና ቤተሙከራውን ለማስፋት እንዲመችም ከአዲስ አበባ ከተማ መሬት አስተዳደር ጋር ዘመናዊ ቤተሙከራ ለመገንባት ሥራዎች ተጀምረዋል። በተለይም ከተማ አስተዳደሩ ቤተሙከራው ከሚገኝበት ሁለት ሄክታር መሬት ላይ አንድ ሄክታር ተጨማሪ በመስጠት ትብብር እንዲያደርግ እየተሰራ ነው። ፈቃደኝነቱም ስላለ በዚህ በኩል ይሳካል። የካናዳ ድርጅትም በተለያየ መልኩ እገዛ ያደርጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ለቤተሙከራ የሚሆን የኬሚካል ግብአት አቅርቦትም ከውጭ ምንዛሪ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በዚህ ረገድ በአገር ውስጥ ለመተካት እድል ይኖራል?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** ክፍተቱ እስካሁን ባያጋጥምም ተግዳሮት መሆኑ ግን አይቀርም። በአገር ውስጥ የሚቀርብ ቢኖርም የግድ ከውጭ መምጣት ያለባቸው ግብአቶች አሉ። እነዚህን መተካት በሚችልበት ሁኔታ ላይ ከወዲሁ መነጋገር ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የጂኦተርማል ወይንም የእንፋሎት ዘርፉ አንዱ የማዕድን ሀብት ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** ዘርፉን በሁለት ከፍለን ማየት ይቻላል። አንዱ ለኤሌክትሪክ ኃይል የሚውልና ሌላኛው ደግሞ ለመዝናኛ የሚውል ነው። ለኤሌክትሪክ ኃይል የሚውለውን እንፋሎት የሚገኝበትን አካባቢና ክምችቱን በጥናት የመለየት ሥራ በማከናወን ለሚመለከተው አካል መረጃ ይሰጣል። በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ከመጡም መረጃውን እንዲያገኙ ይደረጋል። ለአብነትም ኢንስቲትዩቱ ባካሄደው ጥናት መሠረት አሉቶ ላንጋኖና ቱሉሞዬ ላይ የውጭ ባለሀብቶች ገብተው በቁፋሮ ሥራ ላይ ይገኛሉ። አሉቶ ላንጋኖ ላይ ቁፋሮውን እያከናወነ ያለው ኬንጄን የሚባል የኬኒያ ኩባንያ ነው። እስከ 150 ሜጋ ዋት ድረስ መለየት ችለዋል። ቁፋሮው አሁንም ቀጥሏል።

ለመዝናኛ የሚውለውም ቢሆን ወጣቶች ተደራጅተው ለተጠቃሚዎች አገልግሎት የሚሰጡበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ይደረጋል። ለጤናም ሆነ ለመዝናናት ሙቅ ውሃ የሚፈልጉ ሰዎች ብዙ ናቸው፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የገቢ ምንጭ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ምን ምን እቅዶችን አዘጋጅቶች እየሰራ ይገኛል?**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** የሥራ ባህሪው ከሌሎች የሥራ ዘርፎች ይለያል። በዚህ ዓመት ሲጠና የቆየው ሥራ ዓመቱ መጨረሻ ላይ አይጠናቀቅም። በረጅም ጊዜ መንግሥት በውጭ ምንዛሪ ከውጭ የሚያስገባቸውን በአገር ውስጥ ለመተካት የያዘውን አቅጣጫ ማሳካት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስቃስ ምልልሱ ሳደረጉልን ትብብር በእጅጉ እናመሰግናለን።**

**ዶክተር ደጀኔ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እኔና አያቴ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ቁጭ ብያለሁ እየጻፍኩና እያነበብኩ። አያቴ እንደወትሮዋ ለምስራቅ በር ደረቷን ሰጥታ ውጭ አጎዛዋ ላይ ተሰይማለች። አያቴ ውጭ ናት ማለት ፊቷ ላይ ስጥ አለ ማለት ነው..እና ደግሞ ረጅም ሸምበቆ። ከዚህ አለፍ ካለ መቁጠሪያ ብትይዝ ነው። ቀን ሙሉ አልጋዋ ላይ ውላ ጀምበር ወደ ምዕራብ ስታሽቆለቁል አጎዛዋን ይዛ ወደ ደጅ ትወጣለች። የዛን የበግ ይሁን የፍየል የማላውቀውን ገጣባ አጎዛ ከበሩ ደጃፍ በግራ በኩል ካለው ከፍታ ላይ ታደላድልና ትቀመጣለች። ከዛም ዛሬም ድረስ ወዳልደረስኩበት የሀሳብ ባህር ውስጥ ትዘፈቃለች። ስታስብ በጽሞናና ድምጽ አውጥታ ነው። የማይሰሙ ድምጾችን ለራሷ እያወጣች በለሆሳስ ስታጉረመርም ሰምቻት አውቃለሁ። ከሀሳቧ መልስ ማረፊያዋ ብዙ ነው..ከማረፊያዎቿ አንዱ እኔ ነኝ።

‹ፍሰሀ..አንተ ፍሰሀ? ትለኛለች ከሄደችበት የሀሳብ አርምሞ ነፍስ ዘርታ።

‹አቤት! እላለሁ መጽሀፌ ላይ እንዳቀረቀርኩ።

‹ና እስኪ ጀርባዬን እከክልኝ..ማከኪያዬን አጣኋት› ትለኛለች ረጅሙን ሸምበቆ መሬት ላይ እያንደፋደፈች።

የማነበውን መጽሀፍ የቆምኩበት እንዲታወሰኝ ገጹን አጥፌ ወደ ውጭ እወጣለሁ። ‹የቱ ጋ ነው? እላታለሁ የበላትን ቦታ ፍለጋ ጀርባዋን በእጄ እየዳበስኩና በጥፍሬ እየቧጠጥኩ።

‹ዝቅ..ዝ..ዝቅ..ትትትንሽ ከፍ..እ..እእሱጋ› ትለኛለች ጀርባዋን ወዲያና ወዲህ እያስደነሰች..በፍለጋ እያገዘችኝ። አካታለሁ እንደ ጃርት እሾህ በሰላ ጥፍሬ። ሳካት ፊቷ ላይ የእፎይታ መንፈስ አያለሁ። ሳካት ፊቷ ላይ የህመም ስሜት አስተውላለሁ። ከብዙ ማከክ በኋላ ‹ኧረ ቀስ አሳመምከኝ› ትለኛለች ጀርባዋን ከጥፍሬ እያሸሸች። እሷን እያከኩ እኔ አስባለሁ..ከነፍስ መደሰቻዎች አንዱ የበላን ቦታ ፈልጎ ማግኘት ከዛም ማከክ ነው እላለሁ። እንደዛ ባይሆን ያን ሁሉ ደስታ በአያቴ ፊት ላይ አላየውም ነበር። ማከክ ነፍስን መኮርኮር ይመስለኛል..ልብን በሀሴት ማጥመቅ። ማከክ የነፍስን ራቁት ማልበስ ነው እላለሁ። የልብን ባዶነት መሙላት። አንዳንድ ጊዜ ግን ግራ ይገባኛል..የሌሎችን ባላውቅም እኔ ግን አንዳንድ ጊዜ የበላኝን ቦታ ፈልጌ አጥቼው አውቃለሁ። ሆነ የሰውነቴ ክፍል ላይ በልቶኝ ማከክ አሰኝቶኝ የበላኝ ቦታ ግን ይጠፋብኛል። በልጅነቴ ያን ቦታ ፈልጌ ለማግኘት ብዙ ጊዜ ለፍቻለሁ..እሱን ያገኘሁ እየመሰለኝ ያልበላኝን ብዙ ቦታ አክኬ አውቃለሁ።

በዚህ ሀሳብ ውስጥ ሆኜ ለካ ሳላውቀው በኃይል አክኬአት ነበር..በሰላ ጥፍሬ አዛውንት ገላዋን ቧጥጬው ነበር። ጀርባዋን ከጥፍሬ መንጭቃ እያላቀቀች ‹እከከኝ አልኩ እንጂ አቁስለኝ መች አልኩህ? ለራሱ ገላዬ ሳስቷል ያንተ ጥፍር ተጨምሮበት› ስትል ተማረረችብኝ።

ደሞ በሌላ ቀን አጠገቧ ተቀምጫለሁ..የጀመርኩትን የዶክተር አለማየሁ ዋሴን ‹እመጓ› የተሰኘን መጽሀፍ እያነበብኩ። ‹ቆይ ግን መጣፍ አይሰለችህም? ከጠዋት ጀምረህ እንዳቀረቀርክ ይመሽልሀል› ትለኛለች አዛውንት አይኖቿን ወደ እኔ ወርውራ።

‹አሁን እንኳን እያነበብኩ ነው› እመልስላታለሁ።

‹እሱስ ቢሆን ያደክም የለ?

‹ነፍስ የምትወደውን ስትከውን መታደስ እንጂ ድካም አይጎበኛትም። አእምሮ የሚወደውን ሲያስብና ሲሰራ ይበረታል እንጂ አይዝልም። እያደከሙን ያሉ ነገሮች የማንፈልጋቸው ናቸው። ለመኖር ስንል ሳንፈልግ የተጋፈጥናቸው እነሱ› ስል ላሳምናት እሞክራለሁ።

‹በል እንደዛ ከሆነ ደግ! እኔ እኮ እንዲሁ አቀርቅረህ ሳይህ ቢቸግረኝ ነው። ነገ አማኔል ነው አቅም ባገኝ ቤተክሲያን ስሜ ብመለስ ደስ ይለኛል..አታደርሰኝም?

‹አደርስሻለሁ..

‹ጎሽ ተባረክ! ትለኛለች።

አያቴ ከአማኑኤል ጋር ዘውድና ጎፈር ናት..መዳፍና አይበሉባ። ነፍስ እንደዛ ፈጣሪዋን ስታስብ፣ እንደዛ ለፈጣሪዋ ስትገዛ አያቴን ነው ያየሁት። ሳትጠራው ውላ አታውቅም፡ ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነሳ ማታም ወደ መኝታዋ ስትሄድ እያነሳሳችው ነው። የአባት አማኔል የሀገሯ ታቦት ነው..የበቀለችበት፣ የጸደቀችበት፣ የጎመራችበት፣ ሰላሳና ስልሳ መቶም ያፈራችበት የሴትነቷ አልፋና ኦሜጋ።

ውጪ አጎዛዋን ተጋርቼ የባጥ የቆጡን እያወራን ጎን ለጎን ቁጭ ብለናል። እጄን አንገቴ ላይ አሳርፌ እየዳበስኩ ‹ጉሮሮዬን እያመመኝ ነው› እላታለሁ።

‹አ* ላይ ተፍተህ ነው..አ* ማረኝ በል› ትለኛለች።

በዚህ ጊዜ ወዳላባራው ጥያቄዬ እመለሳለሁ። ከዚህ በፊት ይሄን ነገር ብዙ ጊዜ ሰምቼዋለሁ። ለጥያቄዬ መልስ ግን አላገኘሁም። አ* ከአ*..ነት ባለፈ የሆነ ስልጣን የተቸረው መሰለኝ። እውነት ይሁን ውሸት ግን አላውቅም። አያቴ ከዘመናዊው ዓለም ይልቅ ለባህላዊው ዓለም ቅርብ ናት። በዚህና በመሳሰለው እሴቷ ዛሬ ላይ ሳስባቸው የሚያስገርሙኝን ብዙ ነገሮች ነግራኛለች። ለምሳሌ ማታ ቤት አይጠረግም ሲሳይ ይወስዳል። ማታ ጥፍር አይቆረጥም። ማታ ፉጨት አይፏጭም። በማታ መስተዋት አይታይም ብላኛለች።

ጉሮሮዬን እየዳበስኩ ‹አ* ምን ስልጣን ቢኖረው ነው ጉሮሮ የሚያመው? ነው ወይስ እኔ የማላውቀው ስውር ጥበብ አለው? እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ። እውነት ለመናገር እንደ እኔ ለአ* እንክብካቤ የሚያደርግ አለ ብዬ አላስብም። ከሀሳቤ መልስ ‹ግን አ* ከጉሮሮ ጋር ምን አገናኝቶት ነው የሚያመው? ስል ጠየኳት።

‹እኔ ምን አውቄ! ግን እንደዛ ይባላል›።

‹እኔ ግን ምንም አልተዋጠልኝም...

‹አንተ እንግዲህ ሰው የነገረህን አትሰማ..በል እንዳሻህ› ስትል ለፍላጎቴ ትተወኛለች።

ደሞ በሌላ ቀን..ኳስ ስጫወት፣ ስዘል ብቻ በሆነ ምክንያት እግሬ ላይ በተፈጠረ ቁስል መራቢያ አካላቴ ጎን ታፋዬ ስር ህመም ይሰማኛል (በአያቴ አጠራር ንፍፊት ይባላል) እሱን ሰበብ አድርጎ እርምጃዬ ይደነቃቀፋል..ኋያ እንዳሽመደመደው አካል እሽመደመዳለሁ።

‹ምን ሆነህ ነው የምታነክሰው? ትለኛለች እዛው በሯ ደጃፍ ላይ አጎዛዋ ላይ ተቀምጣ..ከወትሮው የተለየ አረማመዴን እያጤነች።

የሆንኩትን እነግራታለሁ..ታፋዬ ስር ህመም እንደተፈጠረ።

‹ንፍፊት ነው! ምን አንተ አርፈህ አትቀመጥ.. ስትንከወከው፣ ከኩሽናው ጣሪያ ላይ ሳር ምዘዝና በእሳት ለኩስና ሰባት ግዜ እርገጥበት ይተውሀል› ትለኛለች እብለት በሌለው ፍጹም እርግጠኝነት።

እንዳለችኝ አደርጋለሁ..ፈጣሪ ምስክሬ ነው ከዛ በኋላ ህመሙ ይለቀኛል። ግን ከጥያቄ አላመልጥም.. የእኔ ህመም ከዛ ሳርና እሳት ጋር ምን አገናኘው ስል ውስጤን እሞግታለሁ። ከሁሉም በኋላ ሕይወት እምነት እንደሆነ ደረስኩበት። ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል አይደል የተባለው? የአያቴ ባህላዊ አተያይ በዘመናዊው ዓለም ተዓማኒነት እንደሌለው ምንም ማረጋገጫ የለኝም። እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ ባህላዊ ልማዶች አሉን። አይናችን ሲርገበገብ፣ መዳፋችንን ሲያሳክከን፣ ውስጥ እግራችንን ሲበላን፣ ምላሳችንን ስንነክስ፣ ስቅ ሲለን በዚህ ሁሉ ውስጥ የምናምነው እምነት አለ።

ኢትዮጵያ ማናት ላለኝ ባላገር ናት ስል እመልስለታለሁ። አዎ ኢትዮጵያ ባላገር ናት። ታሪኳ፣ ባህሏ፣ ስርዓቷ፣ ፖለቲካዋ፣ ኢኮኖሚዋ፣ ማህበራዊ መስተጋብሯ ሁሉ ከገጠር ወደ ከተማ፣ ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ የዘመነ ነው። ከተማ ላይ ስለኖርን፣ ህንጻ ስላየን፣ ከመኪና ጋር ስለተጋፋን ዘመናዊ ነን ማለት አይደለም። ዘመናዊነት በታሪክ ምንጣፍ ላይ መራመድ ነው። የኋላን አለመርሳት ነው። ዘመናዊነት እንደ አያቴ ኢትዮጵያን ማፍቀር ነው። አራዳነት እንደ አያቴ በራስ ታሪክ ውስጥ፣ በራስ ባህል ውስጥ፣ በራስ ማንነት ውስጥ በቅሎ መጽደቅ ነው እያልኩ ብዙ አሰብኩ።

አያቴ ትገርመኛለች..ምንም ልሁን..ምንም ሆንኩ ልበላት መፍትሄ አታጣም። ጤናዳሙን፣ ዳማከሴውን፣ በሶብላውን፣ ግራዋውን፣ ግዛዋውን፣ ሬቱን፣ ባህር ዛፉን፣ ስራ ስሩን፣ ጣዝማ ማሩን፣ የቡዳ መድኃኒቱን፣ እምነቱን፣ ጸበሉን፣ ብቻ በአንዱ ፈውስን ታውቅበታለች። እግዜርን ናት..እንደ እግዜር ናት በእምነትና በኢትዮጵያዊነት ሞልታ የምትፈስ።

# ዓለም አቀፍ




## የኡጋንዳ ፓርላማ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን ወንጀል የሚያደርገውን ሕግ አጸደቀ

የኡጋንዳ ፓርላማ በአገሪቱ ውስጥ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን በእስር የሚያስቀጣ ወንጀል እንዲሆን የሚያደርገውን ረቂቅ ሕግ አጸደቀ። ፓርላማው ማንኛውንም ራሱን በተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት አፍቃሪነት የመደበ፣ ወይም የጾታ ለውጥ ያስደረገ እንዲሁም በእንግሊዝኛ ምሕጻራቸው ኤል-ጂ-ቢ-ቲ-ኪው ዝርዝር ውስጥ የሚካተት የጾታ ዝንባሌ ያለው ዜጋን ሁሉ ወንጀለኛ ያደርጋል። በጸደቀው አዲሱ ሕግ መሠረት የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ያለው ዜጋ ዘለግ ያለ የእስር ጊዜ ይጠብቀዋል።

ይህ ብቻም ሳይሆን ሕጉ እነዚህን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን በጉያው ያቀፈ፣ በቤተሰብ ደረጃ ያስጠለለ፣ ወዳጃቸው የሆነ ወይም አብሯቸው ያለ ሰው "እከሌ እና እከሌ" ብሎ ለሕግ አካላት ማንነታቸውን የማጋለጥ ግዴታን በሌሎች ላይ ይጥላል። በምሥራቅ አፍሪካዊቷ አገር ኡጋንዳ የተመሳሳይ ጾታ ቀድሞም ሕገ ወጥ ተደርጎ ነው የቆየው።

ይህ ሕግ ከሕገ ወጥነቱ አልፎ ነገሩን ወንጀል እና በተራዘመ እስር የሚያስቀጣ ያደርገዋል። በዚህ ወር መጀመሪያ ለፓርላማ የቀረበው ይህ ሕግ በከፍተኛ ድምጽ ነው ትናንት ማክሰኞ የጸደቀው። ከዚህ በኋላ ሕጉን የመሻር ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቬኒ ናቸው። ምናልባት ከምዕራቡ ዓለም ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዳይሻክር እና እርዳታ እንዳይቆም ከፈለጉ ፕሬዚዳንቱ ሕጉ እንዳይጸና ሊወስኑ ይችላሉ።

ካልሆነ ግን ሕጉ ላይ በፈረሙ ቅጽበት ተፈጻሚነቱ ይረጋገጣል። በዚህ ሕግ ልጆችን ለዚሁ ለተመሳሳይ ጾታ ያጨ ወይም ያስተላለፈ የእድሜ ይፍታህ ፍርድ ይጸናበታል። በዚህ አዲስ ሕግ መሠረት በተመሳሳይ ጾታ መብት ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግንኙነቱን የሚያበረታታ ማንኛውንም የሕትመት ውጤት ማተም አልያም በሌሎች የመገናኛ ብዙኃን ማሠራጨት አይችሉም።

ይህን ካደረጉ በሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ። በዑጋንዳ የሚገኙ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ሕጉ በከፍተኛ ሁኔታ ለጥቃት እንዳጋለጣቸው ተናግረዋል። በጎርጎሮሲያውያኑ አቆጣጠር በ2014 ተመሳሳይ ሕግ ጸድቆ የነበረ ሲሆን የዑጋንዳ የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤት ግን ሕጉ ተፈጻሚ እንዳይሆን ወስኖ እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

## የአሜሪካ ባንኮች ፈተና ውስጥ ቢሆኑም ማዕከላዊ ባንክ የወለድ ምጣኔን ከፍ እንዲል ወስኗል



ባንኮች ውድቀት እየገጠማቸው ባለበት ጊዜ የአሜሪካ ማዕከላዊ ባንክ በድጋሚ የወለድ ምጣኔን ጨምሯል። ይህንን እርምጃ መውሰድ የፋይናንስ አለመረጋጋትን ይፈጥራል ከሚለው ስጋት በተቃራኒ ባንኩ እዚህ ውሳኔ ላይ መድረሱ ታውቋል። ማዕከላዊ ባንኩ የባንክ ሥርዓቱ ጠንካራና ችግርን መቋቋም የሚችል ነው የሚል ምክንያት በማስቀመጥ የወለድ ምጣኔውን በ0 ነጥብ 25 በመቶ ከፍ አድርጓል።

ባንኮች እያጋጠማቸው ባለው ኪሳራ ምክንያት በመጪዎቹ ወራት የኢኮኖሚ ዕድገቱን ሊጎዳው እንደሚችልም አስቀምጧል። ማዕከላዊ ባንኩ ዋጋን ለማረጋጋት የብድር ክፍያን እያሳደገ ነው። ሆኖም ከባለፈው ዓመት ወዲህ እየተደረገ ያለው ቀጥተኛ የወለድ ምጣኔ ጭማሪ የባንክ ሥርዓቱ ላይ ጫና አሳድሯል። በዚህም ሳቢያ ሲልከን ቫሊ እና ሲግኒቸር የተባሉ የአሜሪካ ባንኮች ከፍተኛ የወለድ ምጣኔ ባስከተለው ችግር ምክንያት በዚህ ወር ኪሳራ አጋጥሟቸዋል።

የወለድ ምጣኔ መጨመሩ በባንኮች ያሏቸው ቦንዶች ዋጋ እንዲወርድ ሊያደረግ ይችላል የሚል ስጋት ፈጥሯል። ባንኮች ከፍተኛ መጠን ያለው ቦንድ ስለሚይዙ ከፍ ያለ ኪሳራ ላይ የመውደቅ እድል አላቸው። ባንኮች የያያዟቸውን ቦንዶች ለመሸጥ እስካልተገደዱ ድረስ የቦንድ ዋጋ መውረድ በራሱ ችግር አይደለም።

የወለድ ምጣኔ መጨመሩ በሰፊው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ላይ አለመረጋጋትን አያመጣም ብለው የሚያስቡ የበርካታ ሀገራት መሪዎች አሉ። እንደነሱ እምነት ጭማሪው የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት ላይም ተጽዕኖ የለውም። ባለፈው ሳምንት የአውሮፓ ማዕከላዊ ባንክ የወለድ ምጣኔውን በ0 ነጥብ 5 በመቶ ጨምሯል።

የእንግሊዝ ባንክም የዋጋ ግሽበቱ ከባለፈው ወር በ10 ነጥብ 4 በመቶ ባልተጠበቀ ሁኔታ መጨመሩ በተሰማ ማግስት የወለድ ምጣኔ ላይ የሚደረግ ጭማሪን ይፋ ያደርጋል። የአሜሪካ መጠባበቂያ ጽሕፈት ቤት ሊቀ መንበር ጀሮሜ ፖል መሥሪያ ቤታቸው የዋጋ ንረትን መዋጋት ላይ እንደሚያተኩር ገልጸዋል። ሲልከን ቫሊ ያጋጠመወን ችግር ጠንካራ በሆነ የባንክ ሥርዓት ውስጥ የተከሰተ ልዩ ሁኔታ ሲሉ ገልጸውታል።

ሆኖም አሁን ባንኮች ላይ ያጋጠመው ችግር ግን የኢኮኖሚውን እድገት እንደሚጎትት ገልጸዋል። ችግሩ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ሙሉ መልክ ግን እስካሁን ግልጽ አለመሆኑን የቢቢሲ ዘገባ አስታውቋል።

ዜና

# ኅብረተሰቡ ለዓባይ ግድብ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ

- ባለፉት ሰባት ወራት አንድ ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ተሰብስቧል
- “የቦንድ ሳምንት” ከነገ ጀምሮ በአሶሳ ከተማ ይጀመራል

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ ለዓባይ ግድብ ግንባታ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል የግድቡ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ጥሪ አቀረበ። ከሐምሌ 2014 እስከ ጥር 30 ቀን 2015 ባሉት ሰባት ወራትም 989 ሚሊዮን ብር ብር ተሰብስቧል፡፡ ከነገ ጀምሮም በአሶሳ ለአንድ ወር የሚቆይ “የቦንድ ሳምንት” ይጀመራል፡፡

የግድቡ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍቅርተ ታምር ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ የዓባይ ግድብ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ሁለንተናዊ ድጋፍ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ አሁንም ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ሁለት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ መታቀዱን ያስታወቁት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፤ ከሐምሌ 2014 እስከ ጥር 30 ቀን 2015 ባሉት ሰባት ወራት ብቻ 989 ሚሊዮን ብር ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ ውስጥ 98 ሚሊዮን ብሩ በ8100 አጭር የጽሑፍ መልዕክት የተሰበሰበ ነው ብለዋል፡፡

የገቢ አሰባሰቡን ለማጠናከር የተለያዩ መርሐ ግብሮች ሲከናወኑ መቆየታቸውን ጠቁመው፤ በቀጣይነት የሚካሄዱ የተለያዩ ሁነቶች እንደሚኖሩም ጠቁመዋል፡፡

የግድቡ መሠረት ድንጋይ የተጣለበትን 12ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግም ከመጋቢት 16 ቀን 2015 ጀምሮ ለአንድ ወር የሚቆይ «የቦንድ ሳምንት» በአሶሳ ከተማ እንደሚጀመር ጠቅሰው፤ በዚህም 100 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ እቅዱን ማሳካት ይቻል ዘንድ ሁሉም ክልሎች ከዚህ በፊት ሲያደርጉት የነበረውን የማስተባበር ሚና አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ ሀገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ብናልፍም ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ያላሰለሰ ርብርብ የግድቡ ግንባታ ከ90 በመቶ በላይ መጠናቀቁን ያስታወሱት ወይዘሮ ፍቅርተ፤ ኢትዮጵያውያን አሁንም የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም በበኩላቸው፤ የግድቡን ግንባታ ከግብ ለማድረስ ያለምንም የእድሜ ገደብ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እየተሳተፉ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ሕጻናት ሳይቀር የልደታቸውን ወጪ ለግንባታው እየለገሱ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት ከንብረታቸው ላይ ለግድቡ እስከመናዘዝ የደረሱ ግለሰቦች መኖራቸውንም ገልጸዋል፡፡

የዓባይ ግድብ ከግድብነት ባለፈ የሉዓላዊነታችን መገለጫ የሆነ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ፕሮጀክት ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ሁላችንም የየድርሻችንን ኃላፊነት መወጣት አለብን ብለዋል፡፡

በመግለጫው ላይ የተለያዩ ተቋማትና አደረጃጀት ተወካዮች ተገኝተው እስካሁን ሲያደርጉት የነበረውን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ በመጠቆም፤ መላው ኢትዮጵያውያንም ግድቡ ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

የዓባይ ግድብ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ 17 ነጥብ7 ቢሊዮን ብር በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሰብሰቡ ተገልጿል።

# የእምነት ተቋማት

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አንዳንድ ሰዎች ሃገርን እየዘረፉና በማጭበርበርና በማምታታት ብዙ ጥፋት ሲያጠፉ እንመለከታለን»:: አንዳንድ የእምነት አባቶች አጥፊዎችን ገስፆ ከመመለስ ይልቅ የተግባሩ ተሳታፊ ሆነው መገኘታቸው ሀገሪቱን ለችግር የዳረጋት መሆኑንም ጠቅሰዋል::

እንደማኅበረሰብ የጠፋውን የሞራልና የሥነ-ምግባር ከፍታ መልሶ ለመገንባት ቤተ-እምነቶች ያላባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ የተናገሩት ኡስታዝ አቡበከር፤ «ይህንን ሕዝብና ሃገርን እያጠፋ ያለውን የሌብነት ተግባር የሚያስቆም፤ ሕግና ሥርዓት ለማስከበር በሥነ-ምግባሩ የታነፀ ትውልድና ሀገር መፍጠር የሚያስችል ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል» ብለዋል::

ትክክለኛውን ሃይማኖታዊ አስተምህሮና መርሆ ለሕዝቡ በማድረስ፤ ራሳቸውን ከሌብነትና ከመልካም አስተዳደር ችግር በማጥራት፤ ሕግና መርሕን ጥሰው የተገኙ አካላትንም ፊት ለፊት በማጋለጥ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል:: ይህንን ማድረግ ሲቻልም መልካም ስብዕና አጥቶ ወደ ጥፋት የገባውን ትውልድ ለመመለስ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል የሚል እምነት እንዳላቸውም አመልክተዋል::

ኡስታዝ አቡበከር አያይዘውም በተያዘው የረመዳን ፆም ሕዝበ-ሙስሊሙ የአላህ ዋነኛ መርሆ የሆኑትን በተለይም የተቸገሩ፤ የተራቡ፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለአደጋ የተጋለጡትን ዜጎች ዘር ቀለም ሳይለይ ሊደግፍ እንደሚገባ አስገንዝበዋል:: ከዚሁ ጎን ለጎንም የእስልምና ዋነኛ መርሕ የሆነውን ሰላም እንዲሁም የሃገር አንድነትን በማስጠበቅ ረገድ ምዕመኑ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ተናግረዋል::

«ኢትዮጵያ ኅብረ-ብሔራዊ የሆነ የብዝኃነት መገለጫ ያላት ሃገር ናት:: በማንነታችን፤በእምነታችንም ሆነ በሌሎች መገለጫዎቻችን በጋራ እንድንኖር የተወሰነብን ሕዝቦች ነን:: ፈጣሪ በዚህ ሁኔታ እንድንፈጠርና እንድንኖር አድርጎናል» ያሉት መምህሩ፤ ይህችን የጋራ ሃገር አንዱ ለአንዱ እውቅና ሰጥቶና ተከባብሮ መኖር እንደሚገባ አስገንዝበዋል::

አክለውም «ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት ውበት ብቻ ሳይሆን ለሃገራችን እድገት ትልቅ አቅም በመሆኑ ልንጠቀምበት ይገባል» ብለው፤ ልዩነቶች አንዱ የሌላው ደካማ ጎን መሙያ እንጂ ስጋት ወይም መከራ ሊሆኑ እንደማይገባም አሳስበዋል:: «ይህንን ብዝኃነታችንን ተቀብለን ለመሄድ ሁላችንም የጋራ ሥራና ኃላፊነት አለብን፤ በተለይም ቤተ-እምነቶች በዚህ ጉዳይ ላይ በስፋት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል» ሲሉ አፅንዖኖት ሰጥተው ተናግረዋል::


## የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 004/2015

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ፡- Interactive board አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡-

**ስለዚህ፡-**

ጨረታውን ለመጫረት የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች በተገለፀው መሠረት ቀርባችሁ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

1. ተጫራቾች በዚህ የጨረታ ማስታወቂያ የተጠቀሰው interactive board ለመሸጥ በዘርፉ ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው፣ በጨረታ ለመሳተፍ የሚያበቃ ደብዳቤ የያዙና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
2. ማንኛውም ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን በባንክ የተመሰከረ ቼክ (CPO) 10,000.00 ብር (አስር ሺህ ብር ብቻ) ከጨረታ ሰነድ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት።
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል በግዥና ንብረት አስተዳደር ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት 11ኛ ፎቅ በመቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ።
4. ማኛውንም ተጫራች ሰነዱን አሟልተው ኦርጅናል እና ኮፒ ዶክመንቶች በመለየት በታሸገ ፖስታ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በ10 (አስር) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 11፡30 ሰዓት ድረስ በግዥና ንብረት አስተዳደር ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት 11ኛ ፎቅ ለዚሁ የተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለበት ።
5. ጨረታው በ11ኛው ቀን 4፡00 ታሽጎ በዕለቱ ከጠዋቱ 4:30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 11ኛ ፎቅ ላይ ይከፈታል። ሆኖም ቅዳሜ እና እሁድ እንዲሁም የበዓል ቀን ከሆነ በቀጣዩ የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል።
6. የጨረታው አሸናፊ እንደታወቀ ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ (CPO) ለተሸናፊዎች ከ7 ቀን በኋላ ይመለሳል።
7. የጨረታው አሸናፊ በተጫራቾች መመሪያ በተጠቀሰው መሠረት የጨረታ አሸናፊነቱ በጽሑፍ በተገለፀው በ7ኛው ቀን ውስጥ አስፈላጊው የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ወዲያውኑ ወደ ሥራ ክፍሉ መጥቶ ውል መፈፀም አለበት። ይህን ባይፈፅም የጨረታው አሸናፊነቱን በመሰረዝ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል።
8. አሸናፊ ድርጅት ውል ከፈፀመ በኋላ አገልግሎቱን በውሉ መሠረት የሚፈፀም (የሚሰጥ) ይሆናል።
9. ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
10. ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር - 0111-54-14-75/0111-54-19-12 አድራሻ 6 ኪሎ ትምህርት ቢሮ ሕንፃ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ 11ኛ ፎቅ የመንግሥት ግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 11-04 የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 03/2015

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሚ/ር የ8ኛ ዕዝ ለ2015 በጀት ዓመት 2ኛ ተርም ለክፍሉ አገልግሎት የሚውል አላቂ የጽሕፈትና የፅዳት ዕቃዎች፣ የተሽከርካሪና የጀኔሬተር መለዋወጫዎች፣ የዳቦ ማሽን መለዋወጫ፣ የግንባታ መሥሪያ ዕቃዎች፣ የብየዳ ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለሆነም ተጫራቾች አግባብ ያለው የዘመኑ ግብር የተከፈለበት እና የታደሰ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፣ በመንግሥት ግዥ አስተዳደር በአቅራቢዎች ዝርዝር ሊስት ላይ የተመዘገቡና በጨረታ ላይ መሳተፍ የሚያስችል ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ካደራጃቸው አካል ሕጋዊ የትብብር ደብዳቤ ይዞ መምጣት ይጠበቅባቸዋል። ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ከሚያቀርበው ጠቅላላ ዋጋ 2% ማቅረብ ይኖርበታል። ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 15 ቀናት በሰ/ወሎ ዞን ወልዲያ ከተማ ፒያሳ አባይ ኢንሹራንስ ባለው ሕንፃ ውስጥ በሚገኘው ቢሮአችን በመቅረብ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ለዚህ ጨረታ ለተዘጋጀው ሰነድ ክፍያ ፈፅመው ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ። ሲፒኦ ሲዘጋጅ በመከላከያ ሚ/ር ለ8ኛ ዕዝ በሚል ስም ማዘጋጀት ይኖርበታል። ሳምፕል ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ሳምፕል ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ተጫራቾች ለሚያቀርቧቸው ዕቃዎች ዶክሜንቶችን ፋይናንሻልና ቴክኒክል እንዲሁም ኦርጅናል እና ኮፒ ለየብቻው በተለያዩ ፖስታ በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 29/07/2015 ዓ.ም ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ ግዥ ክፍል ዘወትር በሥራ ሰዓት መውሰድና ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ። ጨረታው 29/07/2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ የጨረታ ሣጥኑ ታሽጎ በዕለቱ 8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ለዚሁ በተዘጋጀው ቢሮ በግልፅ ይከፈታል። የ8ኛ ዕዝ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው። ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 0991454479 መደወል ይችላሉ።

**በሀገር መከላከያ ሚ/ር የ8ኛ ዕዝ**
**ወልዲያ**

# ስፖርት



# ከዋልያዎቹ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ምን እንጠብቅ?

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) በ2023 የኮትዲቯር አፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ ዛሬና ከቀናት በኋላ ሶስተኛና አራተኛ የምድብ ጨዋታቸውን ከጊኒ ብሔራዊ ቡድን ጋር ሞሮኮ ላይ ያደርጋሉ።

ዋልያዎቹ ባለፈው ግንቦት ከሜዳቸው ውጭ በመጀመሪያው የማጣሪያ ጨዋታ በማላዊ አቻቸው የ2ለ1 ሽንፈት ቢገጥማቸውም በቀናት ልዩነት እዚያው ማላዊ ላይ የምድቡ ጠንካራ የሆነችው ግብፅን 2ለ0 ማሸነፋቸው ይታወሳል። በዚህም ምድባቸውን መምራት የቻሉ ሲሆን በአፍሪካ ዋንጫ ዳግም ለመታየትም ድንቅ እንቅስቃሴያቸው ተስፋ ጭሮ ነበር። ያም ሆኖ ከረጅም ወራት በኋላ የዚያኔ የነበረው የዋልያዎቹ ስብስብና አሁን ያለው ቡድን ላይ ከወሳኝ ተጫዋቾች በጉዳት ምክንያት ካለመኖር ጋር ተያይዞ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ጥርጣሬና ስጋት መፈጠሩ አልቀረም።



**ዋልያዎቹ ዛሬ ሞሮኮ ላይ ጊኒን በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ወሳኝ ጨዋታ ይገጥማሉ፤**

የአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ስብስብ ቢያንስ አራት ያውም የአጥቂ ስፍራ ወሳኝ ተጫዋቾቹን አጥቶ ነው ጊኒን የሚገጥመው። የቡድኑ ቁልፍ አጥቂ ጌታነህ ከበደ ዋልያዎቹ ፈርኦኖቹን በረቱበት ጨዋታም አልተካተተም ነበር። ጌታነህ ከወራት በፊት ራሱን ከብሔራዊ ቡድኑ በማግለሉም ዋልያዎቹ የእሱን አገልግሎት አያገኙም። ያም ሆኖ ጌታነህ በሌለበት የተሻሉ ግብ አስቆጣሪ ተጫዋቾች ቡድኑን መጥቀም ችለዋል። አቡበከር ናስር፣ ዳዋ ሆጤሳ፣ አማኑኤል ገብረሚካኤል የዋልያዎቹ ወሳኝ ፊታውራሪዎች ቢሆኑም ዛሬ ላይ በጉዳት ምክንያት ከቡድኑ ጋር አብረው አይገኙም። ወትሮም የጨራሽ ተጫዋቾች ክፍት ላለበት የዋልያዎቹ ስብስብ ይህ ትልቅ ጉዳት ነው። አሰልጣኝ ውበቱ እነዚህን ተጫዋቾች ለመተካት አዳዲስ ወጣት ተጫዋቾችን ጭምር ለማካተት ሞክረዋል። አዳዲስ ተጫዋቾች በቡድኑ መካተታቸው ለረጅም ጊዜ እቅድ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ለእንደዚህ አይነት ወሳኝ የነጥብ ጨዋታዎች ነባሮቹን ከአዳዲሶቹ አዋህዶ በአጭር ጊዜ እንዴት ውጤታማ ሊሆን እንደሚቻል ለብዙዎች ጥያቄ ነው። አሰልጣኝ ውበቱም ከርዋንዳው የወዳጅነት ጨዋታ በኋላ የዝግጅት ጊዜ እንዳጠራቸው አልሸሸጉም።

በርዋንዳው የወዳጅነት ጨዋታ ዋልያዎቹ እንደ ቡድን ጥሩ ነበሩ ማለት ይቻል ይሆናል። ግን ብዙ ክፍተቶች እንዳሉባቸው ደግሞ መሸሸግ አይቻልም። አሰልጣኝ ውበቱ ከፍተኛ የተጫዋቾች እጥረት ገጥሟቸዋል። ቡድኑ አሁንም የአጥቂ ችግሩ አልተቀረፈም። ለዚህ ደግሞ አሰልጣኙ እንደ ጌታነህ፣ አቡበከር፣ ዳዋና አማኑኤል ያሉ ተጫዋቾችን ለመተካት የግድ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። በአጥቂ ስፍራ ላይ አንድ መልካም ዜና ቢኖር በኦማን ሊግ ለአል-ሱዋይቅ ክለብ በመጫወት ላይ የሚገኘው ኡመድ ኡኩሪ ከረጅም ጊዜ በኋላ በዋልያዎቹ ስብስብ ውስጥ መካተቱ ነው። ይህ የተሻለ ልምድ ያለው አጥቂ ክለቡ አል-ሱዋይቅ ከቀናት በፊት አል ባሻይርን 4-2 ባሸነፈበት የሊግ ጨዋታ አንድ ግብ ማስቆጠር የቻለ ሲሆን ከወሳኙ አማካኝ ስፍራ ተጫዋች ሽመልስ በቀለ ጋር የሚፈጥሩት ጥምረት የዋልያዎቹን ግብ የማስቆጠር ችግር ለጊዜውም ቢሆን ሊቀርፍ ይችላል ተብሎ ተስፋ እንዲደረግ ያስችላል።

የአማካይ ክፍል ተጫዋቾችን በተመለከተም ኳስን በተገቢ መንገድ ለአጥቂ ከማድረስ ይልቅ ዋልያዎቹ ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ ከማንሸራሸር የቀደመ ልምድ አሁንም መላቀቅ አልቻሉም። ኳስን ተቆጣጥሮ መጫወት ብቻ ደግሞ አስፈላጊውን ነጥብ ሊያስገኝ አይችልም።

የተከላካይ መስመሩን በተመለከተ አላስፈላጊ ኳስ ወደ ኋላ የመመለስ ጉዳይ በርዋንዳው ጨዋታ በተደጋጋሚ ተስተውሏል። ይህ ቡድኑን ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል መሆኑን በበርካታ ጨዋታዎች ታይቷል፣ መታረም አለበት። በተከላካዮች የሚሰሩ አላስፈላጊ ስህተቶችና ጥፋቶችም ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል። በወዳጅነት ጨዋታውም የርዋንዳ ተጫዋቾች የመጠቀም አቅም እንጂ ዋልያዎቹ ግብ ማስተናገድ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነበር። ዋልያዎቹ ዛሬ የሚገጥሙት ርዋንዳን ወይም ሌሎች የምስራቅ አፍሪካ ቡድኖችን ሳይሆን በትልልቅ የአውሮፓ ሊጎች ልምድ ያላቸው ተጫዋቾች ስብስብ ያላት ጊኒን ነው። በዚህ ላይ የጊኒ ተጫዋቾች ፍጥነትን ከአካል ብቃት ጋር ያጣመሩ እንደመሆናቸው ጥቃቅን የተከላካይ ስህተቶችን ተጠቅመው ዋልያዎቹን የመቅጣት እድላቸው ሰፊ መሆኑን ለሰከንድም መዘንጋት አይገባም።

በአንዳንድ ጨዋታዎች የቡድኖች የተጫዋች ጥራት፣ ጥንካሬና ግዙፍ ስም ውጤት ላይወስን እንደሚችል በብዙ አጋጣሚ ተመልክተናል። በዚህ ረገድ ዋልያዎቹ ከሁለቱ የደርሶ መልስ ጨዋታዎች ነጥብ የሚያገኙበት ሌላ እድል ሊኖራቸው ይችላል። ዋልያዎቹ በሁለተኛው የማጣሪያ ጨዋታ የምድቡ ጠንካራ አገር የሆነችው ግብፅን አሸንፈው በመሪነት መቀመጣቸው በስነ ልቦና ረገድ የሚሰጣቸው ጥቅም እንዳለ እውን ነው። ያንን ስነ ልቦና ይዘው በጥሩ የራስ መተማመን ወደ ሜዳ ከገቡ ዝቅ አድርገው የተመለከቷቸው ጊኒዎችን ልክ እንደ ግብፅ ሊቀጡ የሚችሉበት እድል ጠባብ አይሆንም።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት አቶ ዳንኤል ወንድሙ እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ አዲስአለም ዘውዱ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/286615 በ21/10/2014 ዓ.ም እና በኮ/መ/ቁ/30/12/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በለሚ ኩራ /ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር131/06 የሆነው ኮዶሚኒዬም ቤት የቤቱ ስፋት 47.64 ካ/ሜ የሆነ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 612,684 (ስድስት መቶ አስራ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ሰማኒያ አራት ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ 5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሦስት የሥራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ c.p.o ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን።

**በኢፌዴሪ ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይረክቶሬት**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ ኑኑ መኮንን እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ሲሳይ ተስፋዬ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/77560 በ28/8/2013 ዓ.ም እና በኮ/መ/ቁ/83766 በ28/10/2014ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በኮ/ቀ//ክ/ከተማ ወረዳ 06 ሮሆቦት የመኪና ማቆሚያ ግቢ የሚገኝ የሠ/ቁ/ኮድ3-A22781 መኪና የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ) የስም ማዛወሪያ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሚያዝያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ 8:30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሦስት የሥራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ c.p.o ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎች ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን።

**በኢፌዴሪ ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይረክቶሬት**